ሳምንት 12 ማክሰኞ — ሉቃስ 8፥40-56

1. ኢያኢሮስ በይፋ በምን መንፈስ ኢየሱስን ለመነ (ቍ. 40-42)?
2. ሴቲቱ በድብቅ በምን መንፈስ ኢየሱስን ዳሰሰች (42-46)?
3. ኢየሱስ ሴቲቱን በሕዝብ ፊት ለምን አጋለጣት (45-48)?
4. * የኢያኢሮስ ተስፋ፥ ሀ) ኢየሱስን ሲለምን፥ ለ) ኢየሱስ በመንገድ ሲቆይበት፥ ሐ) ሴቲቱ መፈወስዋን ስትገልጥ፥ መ) የልጁን ሞት ሲሰማ፥ ሠ) ኢየሱስ እምነቱ እንዲበረታ ሲያደፋፍረው፥ ረ) ቤቱ ሲገባና፥ ሰ) ኢየሱስ የልጅቷን እጅ ሲይዝ እንዴት እንደተለዋወጠ አሰላስል።
5. ኢየሱስ፥ ሀ) ኢያኢሮስን፥ ለ) ሴቲቱን፥ ሐ) ልጅትዋን እንደየችግራቸው ሲረዳቸው ቸርነቱንና ዘዴውን በማሰብ ጻፍ።
6. ሰዎች በኢየሱስ ያላቸውን ተስፋ እንዲያጠነክሩ ምን ትመክራቸዋለህ?

ቍ.43 ደም የሚፈሳት ሴት፤ በዚህ ሁኔታ «እርኩስ» ነበረችና በሕዝብ መካከል መገባት አይገባትም ነበር (ዘሌ. 15፥19-25)።

ቍ.46 ኃይሉ ከኢየሱስ ከራሱ እንጂ ከልብሱ አልነበረም።

ቍ.48 በሰላም ሂጂ፤ ሴቲቱ በሕዝብ ፊት የነጻች ስለ ሆነች በሰላም መሄድ ቻለች።

ሳምንት 12 ረቡዕ — ሉቃስ 9፥1-27

መግቢያ፤ ኢየሱስ 12ቱን ሐዋርያት በመምረጥ (6፥12-16)፥ ለተወሰኑ መራት ከእርሱ ከተማሩ በኋላ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲሰብኩ ላካቸው ።

1. የሐዋርያት አገልግሎትና አኗኗር ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ሲዘዋወሩ እንዴት ነበረ (ቍ. 1-6)?
2. በዚያን ዘመን ስለ ኢየሱስ ማንነት ምን ዓይነት ሐሳብ ነበረ (7-9፡18-20)?
3. የኢየሱስ ጥንቃቄና ቸርነት በቍ. 10-17 እንደምን ይታያል?
4. ኢየሱስ ስለ ራሱና ስለ ተከታዮቹ ሕይወት ምን ገለጠ (21-27)?
5. ኢየሱስ ሐዋርያትን ለአገልግሎታቸው እንዴት እንዳዘጋጃቸው በመመርመር ስለ አንድ መሪ ምን አርአያነት ታነባለህ (1፡2፡10 ፡13፡18፡21-23)?
6. ራስህን እንዴት ትከዳለህ (23)?

ቍ.20 ከእግዚአብሔር የተቀባህ (የእግዚአብሔር መሢሕ)፤ አይሁድ መሢሑ ከርግውያን ግዛት ነፃ እንዲያወጣቸው ተስፋ ያደርጉ ነበር፥ ኢየሱስ ግን መንግሥቱን በምድር ስለግይመሠርት ከሕዝቡ ራሱን ለይቶ ብቻውን ከሐዋርያት ጋር መሆንን መረጠ (ቍ. 18)።

ቍ.23 መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ፤ ማለት በክርስቶስና በወንጌል ምክንያት የሚደርሰውን መከራ እስከ ሞት ድረስ መቀበል ማለት ነው።

ሳምንት 12 ሐሙስ

ሉቃስ 9፥28-62

1. ኢየሱስ ሲጸልይ ምን ሆነ (ቍ.28-29ን ከ3፥21፤ 6፥12፤ 9፥18 ጋር አወዳድር)?
2. በዚህ ጊዜ የሙሴና የኤልያስ አገልግሎት እንዲሁም ከሰማያት የተሰማው ድምጽ ዓላማ ምን ነበረ (30፡31፡34፡35)?
3. ከቍ.37-56 በሐዋርያት ዘንድ ምን አምስት ስሕተት ይታያል? ከእነዚህ በአንተ ዘንድ የሚገኙትን አመልክር።
4. ኢየሱስ እንዲከተሉት የጠራቸው የምስቱ ሰዎች መልስ ለምን በቂ ሆኖ አልተገኘም (57-62)? ከኢየሱስ አካሄድ ጋር አነጻጽራቸው (51)።

ቍ,30 ሙሴና ኤልያስ፤ ኢየሱስ ሕማንና ክቢያትን ለመፈጸም መጣ። እግዚአብሔር ሕጉን በሙሴ አማካይነት ሰጥቶ ነበር፥ ኤልያስም ከዐበይት (ከታላላቅ) ነቢያት መካከል የመጀመሪያው ነበረ።

9፥51-18፥14 ይህ ክፍል ጌታችን ኢየሱስ ከርስቶስ ከገሊላና ከሰማርያ ከውጣ በኋላ በአገልግሎቱ መጨረሻ ወራት ያደረገውን ይተርካል፤ ሌሎች ወንጌላውያን ስለዚህ ወቅት ብዙ አልጻፉም።

ቍ.52 ሳምራውያን፤ ከ536 ዓመታት ከከርስቶስ ልደት በፊት፥ ከባቢሎን ምርኮ መልስ ጀምሮ በአይሁድና በሳምራውያን መካከል በሃይማኖት ምክንያት ጠብና ጥላቻ ተስፋፍቶ ነበርና ሳምራውያን የራሳቸውን ቤተ መቅደስ በሰማርያ ሠርተው ነበር (ዕዝ.4፥1-5፤ ነህ.2፥20)።

ቍ.59-60 የሰውዬው አባት ገና አልሞተም ነበር፥ ሞቶ ቢሆን ኖሮ በቤት ውስጥ ይገኝ ነበር።

ሳምንት 12 ዓርብ

ኦሪት ዘፍጥረት 37

መግቢያ፤ «የያዕቆብም ትውልድ ይህ ነው» (ቁ.2) በማለቱ የኦሪት ጸሐፊ ወደ አዲስ ክፍል እንደደረሰ ያሳያል። ያዕቆብ ገና በሕይወት ቢኖርም፥ እስከ መጽሐፉ ግብቂያ ያለው ታሪክ የዮሴፍ ነው።

1. ዮሴፍን ወንድሞቹ በምን ሦስት ምክንያቶች ጠሉት (ቍ.1-11)?
2. ዮሴፍ በዚህ ጊዜ እንዴት ያለ ወጣት ነበረ?
3. እንደዚህ ካለ ወጣት ጋር ብትገናኝ ምን ይሰማሃል? ምን ታደርጋለህ?
4. የወንድሞቹ ጥላቻ ወደ ምን ኃጢአት መራቸው (18-35፤ ያዕ.3፥16)?
5. ዮሴፍ ለነጋዴዎች በወንድሞቹ ሲሸጥ ብትገኝ ኖሮ በምን ታጽናናው ነበር? ሰዎች በወንጌል ወይም በጽድቅ ምክንያት ቢጠሉህ ምን መጽናኛ አለህ?
6.* ለተፈጸመው ነገር ሁሉ፥ ሀ)ያዕቆብ፥ ለ)ዮሴፍ፥ ሐ)ሮቤል፥ መ)ይሁዳ፥ ሠ)ሌሎች ወንድሞቹ ምን ያህል ተጠያቂነት ነበራቸው?

ቍ.3 በብዙ ጎብር ያጌጠች ቀሚስ (ጌጠኛ የሆነ እጀ ሙሉ ልብስ)፤ ለሥራ የሚመች ተራ ቀሚስ እጅጌዎች አልነበሩትም፥ በዚህ ቀሚስ ያዕቆብ ለዮሴፍ የነበረውን ልዩ ፍቅር ገለጠ፤ ያዕቆብ በራሱ ሕይወት ከተመሳሳይ አድልዎ የተነሣ ብዙ መከራን ቀምሶ ነበር፤ ነገር ግን የወላጆቹን ስሕተት ደገመ (25፥28)።

ቍ.10 እናትህ፤ በዚህ ልያን ያመለክታል (35፥19)።

ቍ.21 ሮቤል፤ ከወንድሞቹ ታላቅ እንደ መሆኑ መጠን ለዮሴፍ ሕይወት ጎሳፊነት ነበረበት (30)።

ቍ.25፥36 እስማኤላውያን...የምድያም ሰዎች፤ ምድያማውያን ከእስማኤላውያን ጐሳዎች ውስጥ የሚቈጠሩ ናቸው (መሳ.6፥1፤8፥24)።

<u>ሳምንት 12 ቅዳሜ</u> <u>አሪት ዘፍጥረት 38</u>

1. በዚህ ታሪክ የሚገኘው ነውርና ብልግና ሁሉ ከምን ስሕተት የተነሣ ነው (ቍ.1-2ን ከ24፥3፤27፥46፤28፥1 ጋር አነጻጽር)?
2. በሕይወት ጕዞህ ቀላል ስሕተት የመሰለህ ነገር ወደ ብዙ ጕዳት አድርሶህ ያውቃልን?
3. እግዚአብሔር አውናንን ለምን ቀሠፈ (8-10)?
4. ይሁዳ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ውስጥ የወንድንና የሴትን እኩልነት አስተውሎ ነበርን (15-18ን ከ24 ጋር አነጻጽር፤ ሆሴዕ 4፥14 ተመ.)? ይሁዳ እንዳደረገ ሁሉ ዛሬም ለወንድና ለሴት የተለየ ሚዛን የሚያስቀምጡ ይኖራሉን?
5. የትዕግርና የፋሬስ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ለምን ተጻፈ (ማቴ.1፥3)?
6.* በሌላ ሰው ላይ አንድ ነገር በጣም አጸያፊ ሆኖ ቢታይህ በራስህ ሕይወት ላይ ተመሳሳይ ኃጢአት ታስቦህ ያውቃልን? ይህ ዓይነት ሁኔታ በቍ.24 ይታይሃልን? ሕይወትህን በዚህ መሠረት መርምር።

<u>ቍ.8</u> ሕግ በሙሴ ገና ሳይሰጥ፥ አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፥ ወንድሙ በሟቹ ሚስት አማካይነት ልጅ እንዲያቆም ግዴታ ነበረ (ዘዳ.25፥5-6)።

ቍ.9 የአውናን ኃጢአት ዘሩን በመሬት ላይ በማፍሰሱ ብቻ ሳይሆን ለወንድሙ ልጅ እንዳይሰጥ በማድረጉ ነው።

ሳምንት 13 እሑድ

መዝሙር 12(13)

መግቢያ፤ ዳዊት በዚህ መዝሙር «እግዚአብሔር ለምን ይዘገያል?» ለሚለው ጥያቄ የሕይወት ምስክርነቱን ይሰጣል።

1. ዳዊት የጸሎቱ መልስ ሲዘገይበት የመጀመሪያ እርምጃው ምን ነበረ (ቍ.1-4)?
2. ሀ)በቍ.5 እና 6 ስለ እግዚአብሔር የተጻፉትን ምስት ነገሮች ግለጥ፥ ለ)ዳዊት እነዚህን አሰላሰሎ ምን አደረገ?፥ ሐ)ከእነዚህ ቍጥሮች በጸሎት መልስ መዘግየት ስለ እግዚአብሔር ዓላማ ምን ትገነዘባለህ?
3. ሀ)መልስ የዘገየበት ጸሎት ጸልየህ ታውቃለህን?፥ ለ)ችግሩን ወደምትወጣበት እምነት እንድትደርስ ከዳዊት ምን ትማራለህ?
4. ይህ መዝሙር ዛሬ ከምትገኝበት ሁኔታ ጋር አግባብነት ካለው፥ ከፍ ባለ ድምጽ በማንበብ የግልህ ጸሎት አድርገው።

ሳምንት 13 ሰኞ

ኦሪት ዘፍጥረት 39

1. ዮሴፍ ባሪያና እስረኛ ሲሆን መከራውን መታገሥ እንዴት ቻለ (ቍ.2፡21)?
2. ግብጽ አገር ሲደርስ የዮሴፍ፥ ሀ)የሥራ ችሎታ (2-6፡22፡23)፥ ለ)መልክ (6)፥ ሐ)ጠባይ (7-12)፥ መ)እምነት (9) እንዴት ነበረ?
3. በሥራ፥ በትምህርት፥ በስፖርት፥ በሌላም ሙያ ከአንተ በላይ የሚገኙት እንዴት ይመለከቱሃል?
4. ዮሴፍ ከፈተና እንዴት ወጣ (12)?
5. ዮሴፍ በሐሰት ሲከሰስ ምን አደረገ? አንተስ በሐሰት ብትከሰስ ምን ታደርጋለህ? ስለሚከሱህ ምን ይሰማሃል? ይህ ሁኔታ በጸሎትህ ላይ ምን ለውጥ ያመጣል?
6. * የዮሴፍ ሐሳብ ስለ አባቱና ስለ ወንድሞቹ እንዴት እንደነበረ ገምት። እግዚአብሔር በዚህ መከራ ሁሉ ያስተማረው ምን ይመስላል?

ቍ.20 በግዞት ነበረ (በእስር ቤት)፤ መዝ.104(105)፥17-18«እግሮቹ በእግር ብረት ታስረው ነበር፤ በአንገቱም ሰንሰለት ነበረ» ብሎ ሁኔታውን ያብራራል።

ሳምንት 13 ማክሰኞ

ኦሪት ዘፍጥረት 40

1. ዮሴፍ እስረኞችን ያገለገላቸው በምን ዓይነት መንፈስ ነበረ (ቍ.1-7)? የአንተ የአገልግሎት መንፈስ እንዴት ነው?
2. ዮሴፍ ሕልሞቹን በምን አኳኋን ተረጐመ (12-13፡18-19)? ለምን (8)?
3. መንፈሳዊ አገልግሎትህን በጥሩ አኳኋን ለመፈጸም እንደምትችል ሙሉ ተስፋ አለህን? ለምን?

4. ዮሴፍ ከአስር ቤት ለመውጣት እንዴት ምክረ? ከሕይወት ታሪኩ ምን አስቀረ (14-15)? ይህን በመሰለ ሁኔታ ብትገኝ ምን ታደርጋለህ?

5.* ዮሴፍ ገና ምን መማር ነበረበት (14-15፡23)?

ቍ.8 ጉዳዩን ለሕልሞች ትርጉም እንደሚገኝ ያምኑ ነበር። ዮሴፍ (እንደዚሁም ከብዙ ዘመን በኋላ ዳንኤል) የአረማውያንን እምነት ሳይነቅፍ፥ እግዚአብሔርን በሚያስተውሉበት መንገድ ሊናገራቸው እንደሚችል አውቆ ሕልሞቹን ሰምቶ ተረጉመላቸው።

ሰምንት 13 ረቡዕ — ኦሪት ዘፍጥረት 41

መግቢያ፤ ከሁለት ሌሎች ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ከእስር ቤት እንዲፈታ በሩን ለዮሴፍ ከፈተ፤ ሲወጣም ዮሴፍ ለሕይወቱ ሥራ ዝግጁ ሆነ።

1. እግዚአብሔር በላሞቹና በእሸቶቹ ምሳሌነት ለፈርዖን ምን ገለጠ (ቍ.1-32)?

2. ዮሴፍ ትርጉሙን ለፈርዖን በምን አኳኋን ገለጠ (24-26)?

3. ከተጠየቀው ሌላ ዮሴፍ ምን ጨመረ (33-36)? ይህ ስለ ዮሴፍ ምን ይገልጣል?

4. ዮሴፍ ለእህል ሰብሳቢነት ለምን ተመረጠ (37-40)?

5. ሰዎች ምስክርነትህን ይቀበላሉን? ለሹመት ይመርጡሃልን? ለምን?

6.* የዮሴፍ ልጆች ስም ስለ መንፈሳዊ ሕይወቱ ምን ይገልጣሉ?

ቍ.2 ላሞች ከወንዙ ወጡ፤ ከሙቀትና ከተባዮች ነፃ እንዲሆኑ ውኃ ውስጥ ገብተው ይዝሩ ነበር።

ቍ.16 በእኔ አይደለም (ችሎታ የለኝም)፤ እንደ አረማውያን አስተሳሰብ ሕልምን መተርጉም እንደዚሁም ሌላ መንፈሳዊ ችሎታ በሰው እውቀት፥ ጥናት፥ ጥረትና ብልሃት የሚገኝ ይመስላቸው ነበር። እግዚአብሔር ግን የሰውን ማስተዋል ሳይመለከት በወቅቱ ፈቃዱን ይገልጣል።

ቍ.38 የእግዚአብሔር መንፈስ፤ ምንም እንኳን ፈርዖን ከሕግንነቱ ጀምሮ በብዙ አማልክት ቢያምንም፥ ስለ እግዚአብሔር ከተረዳው በላቀ ሁኔታ ተናገረ።

ቍ.45 ጾተፌራ፤ የሄልዮቱ (የአን) ከተማ ካህን ሆኖ ፀሐይን ያመልክ ነበር።

ቍ.46 ሠላሳ ዓመት፤ ወደ ግብጽ ከደረሰ 13 ዓመታት አልፎት ነበር (37፥2)።

ቍ.51-52 ምናሴ፤ «ማስረሻ» ማለት ሲሆን ኤፍሬም «ፍሬአማ» ማለት ነው።

ሳምንት 13 ሐሙስ — ኦሪት ዘፍጥረት 42

መግቢያ፤ ከሃያ አንድ ዓመታት በኋላ ዮሴፍ እንደገና ከወንድሞቹ ጋር ተገናኘ።

1. ወንድሞቹ በሰገዱለት ጊዜ ዮሴፍ ትዝ ያለው ምን ነበር (ቍ.1-9፤ 37፥5-10)? ከዚህስ ምን ተረድቶ ይሆን?

2. ዮሴፍ የወንድሞቹን ኅሊና ለመቀስቀስ ምን አደረገ (6-8፡14-20 ፡25-26)?

3. ዮሴፍ ያደረገው ሁሉ በወንድሞቹ ላይ ምን ለውጥ አመጣ (21-23፡28፡35)?

4. ስትጨነቅ በአስተሳሰብህና በጎሊናህ ምን ለውጥ ይመጣል?

5. በቍጥር 36 ላይ የያዕቆብ ንግግር ትክክለኛ ነውን? ውሉ ሁሉ ቢጠፋብህ ምን ማድረግ ያስፈልግሃል (መዝ.43፡5፤ ሮም 15፡13)?

6.* በኤርምያስ 31፡18-19 እና በዕብራውያን 12፡6 መሠረት የእግዚአብሔርን ሥራ ከዮሴፍ አድራጐት ጋር አነጻጽር።

ቍ,7 ተለወጠባቸውም (በቍጣ ቃል ... ጠየቃቸው)፤ ዮሴፍ ወንድሞቹን ስለወደደ (24) ምንም ሊበቀላቸው አልፈለገም።

ቍ.21 ዮሴፍን ሲሸጡ፡በጓላም ከያዕቆብ ጋር ሲኖሩ ያልተገኘባቸው ርኅራኄ አሁን ይታይ ጀመር።

ቍ.22፡37 ሮቤል፤ ለበኩር ኀላፊነት የበቃ አልነበረም (35፡22፤ 37፡21-22፡29-30፤ 49፡3-4)።

ሳምንት 13 ዓርብ — <u>ኦሪት ዘፍጥረት 43</u>

1. ያዕቆብ ለሮቤል እምቢ ያለውን ለይሁዳ የፈቀደው በምን ምክንያት ይመስልሃል (ቍ.3-10)?

2. እግዚአብሔር ያዕቆብን ምን ያስተምረው ነበር (14)?

3. ልጆችህ ወይም ሌሎች ዘመዶችህን በእግዚአብሔር ስም ለሰው ማስረከብ ተምረሃልን?

4. ወንድሞቹ ወደ ግብጽ ሲወርዱ የነበራቸውን ስሜት ገምት።

5. ዮሴፍ፡ ሀ)ወንድሞቹን (16፡23፡27፡33)፡ ለ)ብንያምን (29፡34) በምን አኳኋን ተቀበለ? ለብንያም አምስት እጅ ለምን ሰጠ?

ቍ,3 ይሁዳ፤ ተሰሚነትን ያገኘና (37፡26፡27) የራሱን ፈቃድ የሚፈጽም ሰው ነበረ (38፡1)።

ሳምንት 13 ቅዳሜ — ኦሪት ዘፍጥረት 44

1. ዮሴፍ የወንድሞቹ ስሜትና አስተሳሰብ በገሐድ እንዲገለጥ ምን አደረገ (ቍ.1-12፡14-15)?

2. ወንድሞቹ ለአባታቸውና ለወንድማቸው በፊት ያልነበራቸውን ርኅራኄ አሁን እንዴት አሳዩ (10፡13፡16)?

3. ቀደም ሲል ወንድሙን በሸጠውና ለአባቱ ባልራራው፡ በይሁዳ ላይ አሁን ምን ለውጥ ይታያል (16-34)?

4. በሰው ፊት ስለማይታወቅ ኃጢአት ምን ታደርጋለህ (16)? አሁን ተናዝዘህ ትገልጠዋለህን ወይስ በእግዚአብሔር እስኪገለጥ ድረስ ትሸፍነዋለህ?

ቍ.5 ምሥጢርንም የሚያውቅበት (ሁሉን ነገር መርምሮ የሚያውቅበት)፤ አስማትና ምዋርት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ተከልክሎ ነበር (ዘኍ.23፡23)። ዮሴፍ የግብጽ ጠቢብ ሰው በመምሰል ይህን የተናገረ ይመስላል።

ቍ.16 እግዚአብሔር የባሪያዎችህን ኃጢአት ገለጠ (እግዚአብሔር የሠራነውን በደል ገልጦታል)፤ ዋንጫውን «መሸረት» ብቻ ሳይሆን በፊት የሠሩትን ኃጢአት ተናዘዙ (42፥21፡22፡28)።

ቍ,33 ይሁዳ በወንድሙ ፈንታ መከራን ለመቀበል ዝግጁ ሆነ።

ሳምንት 14 እሑድ መዝሙር 13(14)

1. ሀ)በዳዊት ዘመን፥ ለ)ዛሬ «እግዚአብሔር የለም» የሚሉ እንዴት ያሉ ሰዎች ናቸው?
2. እግዚአብሔር የሚለምን ሰዎች ሲመረምር ምን ያገኛል?
3. የእግዚአብሔር ሕዝቦች በእነዚህ ሰዎች መካከል ሲኖሩ ምን ተስፋ አላቸው?
4. እንደ መዝሙረኛው ትደሰታለህን? ለምን?

በ1953 ዓ.ም. በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ በመዝሙር 13(14) አሥር ቍጥሮች ሲገኙ፥ በ1980 በታተመው በመዝሙር 14 ሰባት ብቻ ይገኛሉ። ምክንያቱም ይኸኛው ዕብራይስጥን ሲከተል፥ ያኛው ግእዙን ይከተላል። ሆኖም የተጨመሩት ቍጥሮች (13(14)፥ 4-6) ከመዝሙሩ ሐሳብ ጋር ይስማማሉ፥ በሌላም ዘንድ ይገኛሉ (9፥27(10፥7)፤ 35(36)፥1፤ 139(140)፥3፤ ኢሳ.59፥7-8) እና በሮም 3፥13-18 ይጠቀሳሉ።

ቍ.1 ሰነፍ (ሞኝ)፤ በመጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር የለም» ማለት አምላክን ደፍሮ መታወምን እንጂ ሰው በልቡ የሚያስበውን ወይም የምርመራን ጉዳይ አያመለክትም።

ቍ.3 ሁሉ ዐመፁ፤ በቍጥር አንድ የሚገኘው «ሰነፍ» የተባለው ሰውም ከእነዚህ ሰዎች መካከል ነው።

ሳምንት 14 ሰኞ ኦሪት ዘፍጥረት 45

1. ዮሴፍ ማንነቱን ለወንድሞቹ ሲገልጥ ምን ሆነ (ቍ.1-15)?
2. በዚህ ጊዜ የዮሴፍ ዋና ምኞት ምን ነበረ (3፡18፡23)?
3. ወንድሞቹ ወደ ያዕቆብ ሲመለሱ ውይይታቸው ምን እንደነበረ ገምት (24)።
4. ያዕቆብ መልእክቱን በምን አኳኋን ተቀበለ (25-28)?
5. ዮሴፍን ወደ ግብጽ የላከው ማን ነበረ (4-8)? እግዚአብሔር እንዴት ሠራ? ወንድሞቹ ላደረሱበት በደል ተጠያቂዎች ነበሩን?
6. አንተ የምትገኝበትን ሁኔታ እንደ ዮሴፍ ትመለከተዋለህን? ቂም ወይም ቅሬታ አለህን? ለምን?

ቍ,5 የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሰዎች ክፋት ስለማያፋልሰው በክፋታቸው ሂደት እንኳን ዕቅዱን ይፈጽማል (ሐ.ሥ.2፥23፤4፥27-28)።

ቍ.8 ... እናንተ አይደላችሁም፤ እግዚአብሔር የሰውን ክፋት አሸንፎ ለልጆቹ የሚበጃቸውን ሁሉ እንደሚያደርግ በማስተዋል ብቻ ከቂም ነፃ መሆን ይቻላል (ሮም 8፥28)።

ቍ.24 ... አትጣሉ፤ ብዙ ለውጥ በወንድሞቹ ታይቶ ነበር፥ ነገር ግን ምን እንደሆነ ለያዕቆብ ሲገልጡ እርስ በርሳቸው ሊወቃቀሱ ይችሉ ነበር (42፥22)።

ሳምንት 14 ማክሰኞ — አሪት ዘፍጥረት 46

መግቢያ፤ ያዕቆብ ዮሴፍን ለማየት ይመኝ ነበር፥ደግሞም በረሃብ ምክንያት ወደ ግብጽ መውረድ ነበረበት (45፥27-28)። ይህን በማድረጉ አገር እንዲወርስ የተሰጠውን የተስፋ ቃል እንደ መካድ ሊቈጥረው ይችል ነበር። (28፥13-14)፤ ሆኖም ሲጸልይ እግዚአብሔር ፈቀደለት።

1. ያዕቆብ ወደ ግብጽ ሳይወርድ ምን አደረገ? ምን ሆነ (ቍ.1-4)? ያዕቆብ ካሰበው ይልቅ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን ነበረ?
2. በሕይወትህ አንድ ትልቅ ውሳኔ ላይ ከመድረስህ በፊት ምን ታደርጋለህ?
3. ያዕቆብና ዮሴፍ እንደገና ሲገናኙ ምን ሆነ(28-30)?
4. ዮሴፍ የእስራኤል ቤተ ሰብ ከግብጻውያን ጋር ተደባልቆ እንዳይኖር ምን አደረገ (31-34)? ለምን?
5. እንደ ዮሴፍ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ሁሉን በዝርዝር አዘጋጅተህ በማስተዋል ታደርጋለህን? ምሳሌ 13፥16 ተመ.።

ቍ.2 በሌሊት ራእይ፤ ያዕቆብ ወደ ካራን በሸሸ ጊዜ በሕልም (28፥12)፥ አሁን ደግሞ መንፈሳዊ ሰው ሲሆን በራእይ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ራሱን ገለጠ።

ቍ.4 ዮሴፍም እጁን በዓይንህ ላይ ያኖራል (በምትሞትበትም ጊዜ ዮሴፍ ከአጠገብህ ይገኛል)።

ቍ.30 አሁን ልሙት፤ ያዕቆብ ስለ ሞቱ አሁንም እንደገና አሰበ፥አሁን ግን በጭንቀት ፈንታ በልባዊ ሰላም ጠበቀው (37፥35፤42፥38፤44፥29)።

ቍ.34 በግ ጠባቂ ሁሉ ለግብጽ ሰዎች ርኩስ ነው፤ ምናልባት ዘላኖች ስለ ነበሩ ይሆናል።

ሳምንት 14 ረቡዕ — አሪት ዘፍጥረት 47

1. ያዕቆብ በፈርዖን ፊት ሕይወቱን እንዴት ገመገመ (ቍ.7-10)?
2. ግብጻውያን እህልን ለማግኘት ምን አደረጉ (14-15፤ 16-17፤ 18-20፤ 21-24)?
3. ዮሴፍ በአስተዳደሩ ምን መሠረታውያን ሐሳቦችን ይከተል ነበር? እንደ ሕዝቡ ልታመሰግነው ትችላለህን (25-26)?
4. ማናቸውም ዓይነት ጎላፊነት ሲኖርብህ የምትመራባቸው መሠረታውያን ሐሳቦች ምንድን ናቸው?
5. ያዕቆብ ለመሞት ሲቃረብ ምን አደረገ (27-31)? ለምን?

ቍ.24 ከአምስት እጅ አንዱን፤ ለብዙ ዘመን ገበሬዎች ይህን ያህል ለመስጠት እንዴት ይመኙ ነበር!

ቍ,30 ከአባቶቼ ጋር በተኛሁ ጊዜ (በምሞትበት ጊዜ)፤ገና ሳይቀበር ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን አመነ (15፥15፤ ሉቃ.23፥43፤ ፊል.1፥21)።

ቍ.31 በአልጋው ራስ ላይ ሰገደ፤ ወይም የመቋሚያ ጫፍ ተደገፎ ሰገደ፥ ሥራውን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመፈጸም ስለበቃ አመሰገነ። 48፥15ና ግስታወሻ ተመ.።

ሳምንት 14 ሐሙስ — አሪት ዘፍጥረት 48

1. ያዕቆብ አሁን የሕይወቱን ጕዞ እንዴት አስተዋለ (3፡15፡16)? ይህንንም ከአሥራ ሰባት ዓመት በፊት ከሰጠው ግምገማ ጋር አነጻጽር (47፥9)።
2. ስለ ሕይወትህ ምን ዓይነት ምስክርነት ትሰጣለህ? ወደ ሞት ስትቃረብ የአሁኑን ምስክርነት የምትለውጥ ይመስልሃልን?
3. ያዕቆብ ምናሴንና ኤፍሬምን በምን አኳኋን ባረካቸው (13-16)?
4. ዮሴፍ በቡራኬው ለምን አልተደሰተም? ያዕቆብ ምን መልስ ሰጠው (17-20)?
5. ስለ ልጆችህ ወይም ስለ ዘመዶችህ የእግዚአብሔርን ውሳኔ ለመቀበል ያስቸግርሃልን?
6. ያዕቆብ ዮሴፍን እንዴት አጽናናው (21-22)?

ቍ.3 ሉዛ፤ ቤቴል (28፥19)።

ቍ.5 ኤፍሬምና ምናሴ፤ ያዕቆብ ከዔሳው በላይ እንደሆነው ሁሉ፥ ኤፍሬም ታናሹ ቢሆንም ከወንድሙ በላይ እንዲሆን ተመረጠ (25፥23)። ኤፍሬም ከያዕቆብ በዮሴፍ በኩል የበኵሩን መብት ተቀበለ (20፡22፤49፥3-4፤ 1ዜ.መ.5፥1-2)።

ቍ.15 ይህ ቡራኬ የያዕቆብን እምነት ያብራራል። ዕብራውያን 11፥21 ይህን ጥቅስ ከ47፥31 ጋር ያገናኛል።

ቍ.22 ከአሞራውያን ,,, የወሰድሁትን፤ ይህ ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተመዘገበም። ያዕቆብ በልዩ ትግሉ ያገኘውን ቅርስ በመስጠት ለዮሴፍ ያለውን ፍቅር ገለጠ፤ ላደረገለት ውለታም ምስጋናውን አሰማ።

ሳምንት 14 ዓርብ — አሪት ዘፍጥረት 49

<u>መግቢያ</u>፤ የያዕቆብ ልጆችን ቡራኬ ስናነብ ምስት ነገሮችን ልብ ማድረግ ይገባናል፤ 1ኛ. የአባቶቻቸውን እምነት መከተላቸው፥ የተስፋ ቃላትን መቀበላቸውና አንድነታቸው፥ 2ኛ. የአንዳንድ ወንድሞች ኃጢአትና ስሕተት፥ 3ኛ. ለወደፊት የሚናራቸው ጽኑ ተስፋ ከቍጥር 10 በስተቀር ትንቢቱ የሚፈጸመው በተስፋው አገር ነው።

1. ያዕቆብ የሮቤልን፥ የስምዖንን፥ የሌዊንና የዮሴፍን ተስፋ ከጠባያቸው ጋር እንዴት ያገናኘዋል (ቍ.3-7፡22-26)?
2. አንተን በተለይም መንፈሳዊ ጠባይህን በበጎ የሚያውቅ ሰው ምን ተስፋ ይሰጥሃል?
3. ለተከታዮችህ ምን ዓይነት ጠባይ ታወርሳለህ?
4. ስለ ይሁዳ የተሰጠው ትንቢት ከሌሎች በምን ይለያል (8-12)?
5.* የያዕቆብን መንፈሳዊ ዕድገት በቅደም ተከተል ዘርዝር።

ቍ.4 የምትኖላት፤ 42፥22፡27ና ግስታወሻ ተመ.፤ መሳ.5፥15-16።

ኮ.5 የዓመፃ መግሪያ፤ 34፥25-31።

ኮ.7 እበታትናቸዋለሁ፤ የስምዖን ነገድ በይሁዳ መካከል ርስትን አገኘ፤ የሌዊ ነገድ ግን ካህናትና የቤተ መቅደስ አገልጋዮች ሆነው በየአገሩ ተከፋፈር ኖሩ።

ኮ.10 ጎሸ የሆነው ኢሳ መጣ ድረስ («ኢሴ» ተብሎ የሚጠራው ... እስኪመጣ ድረስ)፤ «ሴሎ»፤ ቃሉ በዕብራይስጥ ገልጥ ባይሆንም፥ «ጎሸ በሆነው» ከሕዝ.21፥27 ጋር ይስማማል። ትንቢቱ መጀመሪያ በዳዊት፥በመጨረሻ በክርስቶስ ተፈጸመ (ዘኁ.24፥17)።

ኮ,16-17 ዳን,1 መሳ.18 ተመ.። ነገዱ በራእይ 7፥5-8 አልተጠቀሰም።

ኮ.21 ንፍታሌም፤ መሳ.4፥6፡10፤5፥18፤7፥23።

ሳምንት 14 ቅዳሜ — ኦሪት ዘፍጥረት 50

1. በዮሴፍና በግብጻውያን መካከል የነበረው ግንኙነት እንዴት ነበረ (ኮ.3-11፡21)?
2. ያዕቆብ በምን አኳኋን ተቀበረ (2-3፡12-14)?
3. ዮሴፍ ለምን አለቀሰ (17)? ወንድሞቹ ገና ያልተረዱት ነገር ምን ነበረ (18-20)?
4. ዮሴፍ ከአባቱ ሞት በኋላ 54 ዓመት ሲኖር ተስፋው ምን ነበረ (22-26)?
5. በሕይወትህ ገና የምትጠባበቀው ምን ነገር አለ? እስኪፈጸም ድረስ በሌሎች ላይ አደራ ጥለሃልን?
6. * የዮሴፍን መንፈሳዊ እድገት በቅደም ተከተል ዘርዝር።

ኮ.3 ሰባ ቀን አለቀሱለት፤ ለአንድ ፈርዖን ንጉሥ ሞት ከሚፈጸመው ልቅሶ በሁለት ቀን ብቻ ያነሰ ነበር።

ኮ.24-25 የዮሴፍ እምነት እስከ ፅለተ ሞቱ ድረስ ጸና (ዕብ.11፥22)፤ እንደ መሐላው ተፈጸመለት (ዘጸ.13፥19፤ ኢያሱ 24፥22)።

ሳምንት 15 እሑድ — መዝሙር 14(15)

1. ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ለምን ይከብደዋል?
2. ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በጎበረት እንዲኖር፥ ሀ)በሐሳብ፥ ለ)በቃል፥ ሐ)በአድራጎት መፈጸም የሚገቡትን ነገሮች ዘርዝር።
3. ከተዘረዘሩት ውስጥ በሕይወትህ ማስተካከል የሚገባህን አስምርባቸው።
4. እንግዲህ አሁን ምን ታደርጋለህ?

ኮ,1 በድንኳንህ (ወደ መኖሪያህ) ... በተቀደሰው ተራራ፤ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር መጀመሪያ የተገናኘው በመገናኛው ድንኳን በኋላም በኢየሩሳሌም በተመራው በዚተ መቅደስ ነበረ።

ኮ,5 በአራጣ የማያበድር (ያለ ወለድ የሚያበድር)፤ በእስራኤል ማበደር ችግረኞችን ለመርዳት እንጂ ለማትረፊያ አይፈቀድም ነበር። የኔታ ኢየሱስ ሐሳብ ግን ከዚህ ይልቃል (ሉቃ.6፥35)። እስራኤል ለሌላ ሕዝብ እንዲያበድር ተፈቅዶለት ነበር (ዘዳ.23፥20፤ ማቴ.25፥27)።

ሳምንት 15 ሰኞ — ሉቃስ 10፥1-24

መግቢያ፤ ኢየሱስ በገሊላ ሥራውን ከጨረሰ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ለሕማማቱ ሳይወጣ በይሁዳና በፓርያ የመንግሥቱን ወንጌል በፍጥነት ለማስፋፋት ወሰነ።

1. ኢየሱስ ዓላማውን ለመፈጸም ምን አደረገ (ቍ. 1-2)?
2. የሰባው ደቀ መዛሙርት ተልእኮ ዓበይት ጠባያት ምን ምን ነበሩ (1-9)? ለሥራህ አስፈላጊ የሆኑትን አስምር።
3. የአድማጮቻቸው ፍርድ በምን ላይ የተመሠረተ ነው (10-16)?
4. ሰባው ወንጌላውያን ከስምሪት በኋላ በደስታ ሲመለሱ ኢየሱስ ስለ ሥራቸው ምን መከራቸው (17-24)? ለምን?
5. ሥራህ ሲከናወንልህ ምን መገንዘብ ይኖርብሃል?
6.* ቍጥር 21 እና 22 ስለ አብና ወልድ ግንኙነትና ተግባር ምን ይገልጻል?

ቍ. 12 ሰዶም፤ ዘፍ. 13፥13፤ 18፥20-19፥29።

ቍ. 13 ኮራዚን ...ቤተ ሳይዳ፤ ከቅፍርናሆም ያልራቁና በገሊላ ባሕር ዳር የነበሩ ከተሞች።

ቍ. 14 ጢሮስ ..,ሲዶና፤ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ፍርድ የተነበዩባቸው የታላቁ ባሕር ወደቦች።

ቍ. 18 ሰይጣንን ...ሲወድቅ አየሁ፤ ሰባዎቹ ደቀ መዛሙርት (አርድእት) በየምሥራች ተልእኮአቸው አጋንንትን ሲያወጡ ኢየሱስ የሰይጣንን ውድቀት ይመለከት የነበረ ይመስላል።

ሳምንት 15 ማክሰኞ — ሉቃስ 10፥25-42

1. የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት የሙሴ ሕግ ምን ይጠይቃል (ቍ. 25-28)?
2. ሀ)ካህኑ፥ ለ)ሌዋዊው የተደበደበውን ሰውዬ ላለመርዳት ምን ሰበብ ነበራቸው?
3. ከእነዚህ የሃይማኖት ሰዎች ሳምራዊውን ልዩ ያደረገው ምን ነበር?
4. ዛሬ ሰውን ለመርዳት ምን ታደርጋለህ?
5. በጥሞና ማምለክንና በትጋት ማገልገልን ሚዛናዊ በሆነ መልክ መያዝን ለምደሃልን (38-42)? በዘወትር ሕይወትህ ቅደም ተከተሉን እንዴት ታውቃለህ?

ቍ. 30 ኢያሪኮ፤ ብዙ ካህናትና ሌዋውያን የኖሩበት፥ ከኢየሩሳሌም 27 ኪ.ሚ. የሚርቅና አንድ ሺህ ሜትር ዝቅ ያለ በዮርዳኖስ ሸለቆ የሚገኝ ከተማ።

ቍ. 32 ሌዋዊ፤ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ሥርዓት፥ ካህናትን ለማገልገል መብት ከነበረው ከሌዊ ነገድ።

ቍ. 33 ሳምራዊ፤ 9፥52ና ማስታወሻ ተመ.። መምህሩ ይህን አጸያፊ ቃል ከመናገር ተቆጠበ (37)።

ቍ. 34 ዘይትና የወይን ጠጅ፤ በዚያ ዘመን የተለመዱ መድኃኒቶች።

ቍ.35 ሁለት ዲናር (ሁለት ብር)፤ ለብዙ ጊዜ ማስተናገጃ የሚበቃ የወታደር የሁለት ቀን ደመወዝ።

ሳምንት 15 ረቡዕ ሉቃስ 11፥1-13

1. ደቀ መዛሙርቱ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በምን መሠረት ተጋበዙ (ቍ.2፡13)? አንተስ?
2. በቍ.2-4 የሚገኙትን የጸሎት ጥያቄዎች ዘርዝር፤ ከቅደም ተከተላቸው ለጸሎትህ ምን መመሪያ ታገኛለህ?
3. ከእነዚህ የጸሎት ምሳሌዎች፥ ሀ)ስለ እግዚአብሔር፥ ለ)ስለ ጸሎት መልስ ምን ትማራለህ (5-13)?
4. ነዝንዘህ ትጸልያለህን? ለምን?

ቍ.2-4 ከግቴ.6፥9-13 ጋር አነጻጽር።

ቍ.2 ስምህ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ስም ሲጠቅስ ባሕርዩን ያመለክታል።

ቍ.8 ንዝንዛው፤ በእኩለ ሌሊት ቢሆንም ወዳጁ በመሆኑ የፈለገውን እንደሚቀበል በግሙን አስቦገረው።

ሳምንት 15 ሐሙስ ሉቃስ 11፥14-36

1. ሰዎች ተአምሩን ሲያዩ ምን አደረጉ (ቍ.14-16)?
2. ኢየሱስ «በሰይጣን ኃይል አጋንንትን ያስወጣል» የሚለውን ሐሳብ ውድቅ ለማድረግ ምን ምክንያት አቀረበ (15-22)?
3. ሰው ከክርስቶስ ጋር ሲገናኝ ውሳኔ ላይ ሳይደርስ መቆየት እንደማይችል እንዴት አስጠነቀቃቸው (23-28)?
4. የኢየሱስ ዘመን ሰዎች፥ ሀ)ክፋት፥ ለ)ዝንባሌ ምን ነበረ (16፡29-32)?
5. ሰዎች በተለያየ ምክንያት ኢየሱስን ባለመቀበላቸው ስለ ራሳቸው ምን ይገልጣሉ (15-16፡33-36)?
6. የዛሬ መሪዎችን «ብርሃን» (አመለካከት) ከኢየሱስ ትምህርት ጋር አነጻጽር።

ቍ.15 ብዔል ዜቡል፤ የአጋንንት አለቃ፥ ሰይጣን። በዘመናዊ ቋንቋ «የቤት ባለቤት» የነበረ ይመስላል(21)።

ቍ.30 ዮናስ፤ በነነዌ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለመናገር የተላከ የእስራኤል ነቢይ። የነነዌ ሰዎች ከሙታን እንደተነሣ ሰው ቁጥረው መልእክቱን እንዳመኑበት ሁሉ፥ ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ብዙዎች በይበልጥ አመኑበት።

ቍ.32 ... ከዮናስ የሚበልጥ፤ ኢየሱስ ከሰይጣን ኃይል (22)፥ ከሰሎሞን ጥበብ (31) እና ከዮናስ ተልእኮ የእርሱ እንደሚልቅ ገለጠ።

ሳምንት 15 ዓርብ ሉቃ.11፥37-54፤ 12፥1-3

1. የፈሪሳውያንን ስሕተት አንድ በአንድ ዘርዝረህ አብራራ (ቍ.37-44)።
2. ፈሪሳዊነት በአንተ ዘንድ እንዳይገኝ ምን ታደርጋለህ?

3. የሕግ አዋቂዎቹ ምስጉ ስሕተቶች ምን ነበሩ (45-52)?

4. የዛሬ «ሕግ አዋቂዎች» ምን ያስተምራሉ?

5. ኢየሱስ «ወዮላችሁ» በማለት የሃይማኖት መሪዎችን ስንት ጊዜ ወቀሰ? ይህ ስለ ፍርዳቸው ምን ያሳያል (48-50)?

6. ኢየሱስ በዚህ ወቅት ደቀ መዛሙርቱን ማበረታታት ለምን አስፈለገው (53-54)? እንዴትስ አበረታታቸው (12፥1-3)?

11፥38 አስተድሞ እንዳልታጠበ (እጁን ስላልታጠበ)፤ ይህ ከቀሻሻ (እድፍ) መንጻትን ሳይሆን፥ አንድ አይሁዳዊን ለምሳሌ አንድ ከአሕዛብ መንን የሆነ ሰው በድንገት ቢነካው እንደ ሥርዓታቸው እንዲነጻ ይደረግ ነበር።

11፥44 የተሰወረ መቃብር፤ አይሁድ ሰዎች መቃብሮችን በመንካት እንዳይረክሱ ምልክት ያኖሩባቸው ነበር (ዘኁ.19፥16)።

11፥51 አቤል ... እስከ ዘካርያስ፤ በአይሁድ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቅደም ተከተል ዜና መዋዕል የመጨረሻው ነበር፥ ስለዚህ አቤልን እንደ መጀመሪያው ሰማዕት፥ ዘካርያስንም እንደ መጨረሻ ይቁጥሩ ነበር (ዘፍ.4፥4-8፤2ዜ.መ.24፥20-22)።

ሳምንት 15 ቅዳሜ — ሉቃስ 12፥4-34

1. ሀ)የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በግልጥ ሲመሰክሩ እንዳይፈሩና እንዳይጨነቁ ምን ምክንያት አላቸው (ቍ.4-12)?፥ ለ)ማንን መፍራት ይገባቸዋል (5፡9-10)? ለምን?

2. ሀብታሙ ሰውዬ ትላልቅ ጉተራዎችን በመሥራቱ ተጨንቶ ነበርን (16-20)? ኢየሱስን የጠየቀው ሰውዬና የሀብታሙ ስሕተት ምን ነበረ (13-15፡21)?

3. ደቀ መዛሙርት በሀብት እጦት እንዳይጨነቁ የተሰጣቸውን ምክንያት ዘርዝረህ ጻፍ (22-30፡32፡34)።

4. ምን ማድረግ ይገባቸዋል (31-34)?

5. ኢየሱስ በአካለ ሥጋ በአጠገብህ ቢኖኝ ኖሮ ስለ ፕንጩህ ምን ይመክርህ ነበር?

ቍ.10 መንፈስ ቅዱስን የሚሰድብ ግን እደለረዳለትም፤ ክርስቶስ በመለኮታዊ ክብር ለሰው ዐይን ስላልተገለጠ ሰው ሳያስተውል ስለ እርሱ የሚያጣውን ታል መናገር ይችል ነበር፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገር ግን አውቆ እግዚአብሔርን ስለሚክድ ይቅር አይባልለትም።

ቍ.28 ግር፤ ለማገዶ ይጠቅም ነበር።

ሳምንት 16 እሑድ — መዝ.15(16)

1. የአማኙ፥ ሀ)ጠባይ (ቍ.1-4)፥ ለ)እድል (5-8)፥ ሐ)ተስፋ (9-11) ምንድን ነው?

2. ዳዊት ስለ ሌሎች የነበረውን ስሜት ከራስህ ጋር አነጻጽር (3-4)።

3. አንተ አሁን በምትገኝበት ሁኔታ እንደ ዳዊት ትደሰታለህን (5-9)? ለምን?

4. የዳዊት ተስፋ እንዴት ተፈጽሞአል (ሐ.ሥ.2፥25-27፤ 13፥35)?

5. ይህ ትንቢት በክርስቶስ ትንሣኤ በመፈጸሙ ምን ተስፋ አግኝተህበታል?

6. እንደ ዳዊት በእግዚአብሔር መተማመንህ ምን ለውጥ ያመጣልሃል?

ሥ.ሐ 2፡25-28 ጌታ ሁልጊዜ፣ ለዳዊት እግዚአብሔር የሰጠው አገር መልካም ቢሆንም ወይኑቱኛ ቢኖር ለእርሱ እግዚአብሔር ሥሉ እንደነበረ ሁሉ ሰዳዊትም ሀገ (ዘኁ.18፡20)።

ሳምንት 16 ለሽ ሉቃስ 12፡35-59

ርዕሰጉዳይ፣ ኢየሱስ ስለ መገዛሙ ከተናገረ በኋላ (12፡31-33) ስለ ዓለም ምጽአቱ ተናገረ።

1. ጌታው ሲመጣ፡ ሀ)ዝግጁ የሆኑ፡ ለ)ዝግጁ ያልሆነ ሰው ጠባይ እንዴት ያለ ነው (ቍ.35-48)? አድራጎታቸውን ቍ.34 እንዴት ያብራራል?

2. እነዚህ ምስት ምሳሌዎች፡ ሀ)ስለ ጌታ መመለሻ ወቅት፡ ለ)ለታማኞች ስለሚሰጠው ዋጋ፡ ሐ)ያልታመኑትም ስለሚደርስባቸው ቅጣት ምን ያስተምራሉ?

3. ኢየሱስ ሕማማቱን በተመለከተ፡ ሀ)ለደቀ መዝሙርት (49-53)፡ ለ)ለተራው ሕዝብ (54-59)፡ ምን ማስጠንቀቂያ ሰጠ?

4. ለጌታ ዳግም ምጽአት ዝግጁ ለመሆን ምን ታደርጋለህ?

ቍ.35 ወገባችሁ የታጠቀ (በአጭር ታጥቃችሁ)፤ ረጅም ልብስ ለሥራ አያመችም።

ቍ.50 የምጠመቃት ጥምቀት (የምጠመቀው የመከራ ጥምቀት)፤ ጥምቀት፡በውኃ፡ በመንፈስ ቅዱስም ሆነ፡በሥቃይ፡ወደ አዲስ ሁኔታ ይመራል። ኢየሱስ በአንድ በኩል ስለ ሕማማቱ ሲጨነቅ በሌላ በኩል ደግሞ መሬጸሙን ይመኝ ነበር።

ቍ.57-58 ራሳችሁ .., ባላጋራህ፤ እያንዳንዱ ሰው ወደ ፍርድ ሳይደርስ ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅን ማግኘት ይኻለዋል።

ሳምንት 16 ማክሰኞ ሉቃስ 13፡1-21

1. ሰው በድንገተኛ አደጋ እንደሞተ ስትሰማ ምን ማሰብ ይገባሃል (ቍ.1-5)?

2. ቍ.9ን ከ3 እና 5 ጋር በማነጻጸር፡ የበለስ ምሳሌ ቍ.1-5ን እንዴት እንደሚያብራራ ግለጥ።

3. የሴቲቱን ሁኔታና ፈውስ ማግኘቷን ከታሰሩት እንስሳት ጋር አነጻጽር (10-17)።

4. የሰናፍጭና የእርሾው ምሳሌዎች ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት ምን ያስተምራሉ (18-21)?

5. የሰውየውና የሴቲቱ ፈንታ ምን ነበረ? የእንተስ?

ቍ.1 በዚያን ጊዜ ...፤ ኢየሱስ በ12፡59 ምክር ላይ ለግተኩር በአጋጣሚ የሰማውን ነገር ተጠቀመ።

ጲላጦስ፤ ጨካኝ ሰው ነበረና በግዛቱ ብዙ ሰዎች በግፍ ሞቱ።

ቍ.4 በሰሊሆም ግንብ፤ ከሰሊሆም መጠመቂያ ያልራቀ፡ በኢየሩሳሌም ገድግዳ ላይ የነበረ አንድ ግንብ ይመስላል።

ቍ.10 በሰንበትም በአንድ ምኵራብ፤ ኢየሱስ ከዚህ በኋላ እንደገና በምኵራብ ስለ መገኘቱ በአራቱ ወንጌል አልተጻፈም። ጠላቶቹ እስከ መጨረሻው ቢቃወሙትም (14) መንግሥቱ እየተስፋፋ ሔደ (17-21)።

ሳምንት 16 ረቡዕ — ሉቃስ 13፥22-35

1. በኢየሱስ ትምህርት መሠረት ማን ሊድን ይችላል (ቍ.22-24)?
2. ጠባቡ በር በመዘጋቱ፥ የሚደነግጡት ሰዎች የማያስተውሉት ነገር ምንድን ነው?
3. የቍ.28-30 ትምህርት ለአይሁድ ለምን ይከብዳል?
4. እንደነዚህ «ዓመፀኞች»፤ ብዙዎቹ የዛሬ የቤተ ክርስቲያን አባሎች ተስፋ ባዶ ሊሆን ይችላልን? የአንተን ተስፋ ሕያው የሚያሰኘው ምንድን ነው?
5. ኢየሱስ ሄሮድስንና ሥልጣኑን እንዴት ተመለከተ (31-33)?
6. ቍ.34 ስለ ኢየሱስ ምን ይገልጣል?

ቍ.22 ወደ ኢየሩሳሌም ሲሔድ፤ 9፥51፤ 10፥1።

ቍ.31 ሄሮድስ፤ 3፥1 እና የ3፥1-20ን መግቢያ ተመ.።

ቍ.32 ቀበር፤ በአይሁድ የተንኰለኛና የምናምንቴ ሰው ምሳሌ።

በሦስተኛው ቀን፤ በአይሁድ አባባል አንድ ነገር የሚፈጸምበትን ወቅት ሊያመለክት ይችል ነበር።

ቍ.35 ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም፤ ከሕግማቱ በኋላ እስከ ዳግም ምጽአቱ ድረስ ለአይሁድ ራሱን አይገልጥም (ሮም 14፥11፤ ፊል.2፥10-11)።

ሳምንት 16 ሐሙስ — ሉቃስ 14፥1-35

መግቢያ፤ ኢየሱስ በሰንበት ለምሳ ግብዣ በአንድ ፈሪሳዊ ሲጠራ ስለ ልዩ ልዩ ነገር ለመናገር አጋጣሚውን ተጠቀመ።

1. ኢየሱስ ስለ፥ ሀ)ሰንበት (1-6)፥ ለ)ትሕትና (7-11)፥ ሐ)ለግብዣ ሰዎችን ስለ መጥራት (12-14) ምን አስተማረ?
2. አንተ ግብዣን ስታዘጋጅ ዓላማህ ምንድን ነው?
3. ዛሬ ሰዎች የወንጌልን ጥሪ ላለመቀበል የሚያመካኙበትን ከቍ.18-20 ጋር አነጻጽር።
4. አገልጋዩ የጌታን ፈቃድ ለመፈጸም ምን አደረገ (17-24)? አንተስ?
5. ማንኛውም ሰው ክርስቶስን ለመከተል ከመወሰኑ በፊት ምን መረዳት አለበት (25-35)?

ቍ.1 እንጀራ ሊበላ፤ 7፥36፤ 11፥37 ተመ.።

ይጠባበቁት ነበር፤ 6፥1-11፤ 13፥10-17 ተመ.።

ቍ.26 ... ባይጠላ (ከኔ አብልጦ የሚወድ ከሆነ)፤ ከሁሉ በፊት የክርስቶስን ፈቃድ ማስቀደም ያስፈልጋል።

ሳምንት 16 ዓርብ

ሉቃስ 15፥1-10

መግቢያ፤ ጌታ ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ሳይሆን ኃጢአትን ይጠላል፤ ኃጢአተኞችን ባለመናቁም ወደ ቤታቸው ገባ፥ አብሮአቸውም በላ ጠጣ። በዚህም. እግዚአብሔር ንስሐ የሚገባ ኃጢአተኛን በደስታ እንደሚቀበል በምሳሌዎች አስተማረ።

1. ኢየሱስ እነዚህን ምሳሌዎች ለማን ተናገረ (ቍ. 1-2)? ለምን?
2. እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች፥ ሀ)ማንኛውም ኃጢአተኛ በክርስቶስ ዘንድ ፍቅር እንዳለው፥ ለ)የጠፋውን ኃጢአተኛ ለመመለስ ከፍተኛ መሥዋዕትነት እንደሚጠይቅ፥ ሐ)የጠፋው ኃጢአተኛ ወደ እግዚአብሔር ቤት ሲመለስ ምን ያህል ደስታ እንደሚሆን . . . እንዴት ያብራራሉ?
3. ኃጢአተኞችን ባገኘህ ቍጥር ምን ይሰማሃል? ንስሐ እንዲገቡ ምን ታደርጋለህ? በእውነት ትወዳቸዋለህን?

ቍ. 1 ቀራጮች፤ እንደ ዋና ኃጢአተኞች ይቈጠሩ ነበር። የ3፥17 ግስታወሻ ተመ.። ቍ. 8 ድሪም (የወርቅ መሐለቅ)፤ በጋብቻ ጊዜ ከተሰጣት ጥሎሽ ውስጥ ሊሆን ይችላል።

ሳምንት 16 ቅዳሜ

ሉቃስ 15፥11-32

1. ሀ)የልጁ ሐሳብ ከቤቱ ሲወጣና ወደ ቤቱ ሲመለስ እንዴት እንደነበረ አነጻጽር (ቍ. 12፥13፥18፥19)፥ ለ)በጠባዩ መሠረታዊው ለውጥ ምን ነበረ (17-18)?
2. ሐሳቡን የለወጠው ምን ነበረ (14-17)? በአንተ ወይም በሌላ ሰው ይህን የመሰለ ጠባይ አይተሃልን?
3. አባትዬው ልጁን በምን አኳኋን ተቀበለው (20-24)? ክርስቶስ በዚህ ዓይነት እንደተቀበለህ ታውቃለህን?

4. ታላቁ ልጅ በአባቱ ላይ በግልጽ ለማመጽ የፈራ ይመስልሃልን? እርሱስ ንስሐ መግባት ያስፈልገዋልን?

5.* ታላቁ ልጅ ከፈሪሳውያንና ከጻፈዎች ጠባይ ጋር በምን ይመሳሰላል (2፡25-32)?

ቍ.15 እሪያ፤ አሳማ በአይሁድ ዘንድ ርኩስ ነበረና እሪያን መጠበቅ ትልቅ ነውርና ውርደት ነበረ።

ሳምንት 17 እሑድ — መዝሙር 16(17)

1. በዚህ መዝሙር የዳዊት ምስት ዐበይት ልመናዎች ምንድን ናቸው (ቍ.1-5፡6-12፡13-15)?

2. ለእያንዳንዱ ልመና ምን ምክንያት አቀረበ?

3. በእውነት በቍጥር 1-5 እንዳለው መጸለይ ትችላለህን? እንዴት?

4. መዝሙሩ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይገልጣል?

5. በቍጥር 15 ያለው የዳዊት ተስፋ የአንተም ነውን? ለምን?

ሳምንት 17 ሰኞ — ሉቃስ 16፡1-15

1. ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ለማን ተናገረ (ቍ.1)?

2.* የዚህ ምሳሌ የአተራረክ መንፈስ እንደ «የጠፋው ልጅ» ምሳሌ ከባድ ነው ወይስ ቀላል?

3. ጌታው ለምን መጋቢውን «አመሰገነው» (8)? መጋቢው ለክርስቶስ ተከታዮች በምን በኩል ጥሩ ምሳሌ ሆነ(8-9)?

4. ኢየሱስ ምሳሌውን በሌላ መንገድ በመጠቀም ስለ ሰው ታማኝነትና ጎላፊነት ምን አስተማረ (10-13)?

5. ይህን የሰሙ ፈሪሳውያን ሲያፌዙ፡ ስለ ገንዘብ የነበራቸውን ሐሳብ ለመለወጥ ኢየሱስ እንዴት ሞከረ (14-15)?

6. አንድ ሰው የገንዘብ አጠቃቀምህን አይቶ ስለ አንተ ምን ይመሰክር ይሆን?

ቍ.14-15 ገንዘብን የሚወዱ ፈሪሳውያን፤ የገንዘባቸው ክምችት፡ ሕግን ከመጠበቅ የተገኘ ዋጋ ነው በማለት ያስቡ ነበር።

ሳምንት 17 ማክሰኞ — ሉቃስ 16፡16-31

1. ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ትምህርት ከሕግ ጋር እንዴት አያያዘው (ቍ.14-17)?

2. የሁለቱን ሰዎች ሁኔታ ከሞት በፊትና ከሞት በኋላ አነጻጽር (19-23)።

3. ሀብታሙ በምን ምክንያት ተቀጣ? ቍ.25ን ከ15፡2 እና ከ16፡14-18 ጋር አያይዝ።

4. ቍ.31 ስለ ሰው ፈቃድ ምን ይገልጣል?

5. በዚህ ዓለም የምትሠራው ሁሉ በሚመጣው ምን ውጤት ያመጣል?

6.* ይህ ምሳሌ፥ ሀ)ስለ መዳን ጊዜ (26)፥ ለ)ስለሚመጣው ፍርድ (24-28)፥ ሐ)ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣንና ብቃት (29-31) ምን ያስተምራል?

ቍ.18 ሚስቱንም የሚፈታ . . .፤ ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን ዘመንም የሕግን ትእዛዛት መፈጸም እንደሚያስፈልግ ያሳያል። ፈሪሳውያን በብዙ መንገድ ሕግን በጥብቅ ለማክበር ቢሞክሩም በፍች ልማዳቸው እጅግ ልል ነበሩና በሕግ መኮራራታቸው ከንቱ መሆኑን ገለጠ (ቍ.14-15ና ማስታወሻ ተመ.፤ ማቴ.19፥3-12)።

ሳምንት 17 ረቡዕ — ሉቃስ 17፥1-19

መግቢያ፤ ኢየሱስ የፈሪሳውያንን ጠባይ ሳይረሳ ከዚሁ አንጻር በደቀ መዛሙርት ላይ ሊገኝ የሚገባውን መንፈስ አብራራ።

1. ኢየሱስ ስለ ደቀ መዛሙርቱ፥ ሀ)ኀላፊነት (ቍ.1-2)፥ ለ)ይቅር ባይነት (3-4)፥ ሐ)እምነት (5-6)፥ መ)የአገልግሎት መንፈስ (7-10) ምን አስተማረ?
2. ኀላፊነትህን ለመፈጸምና ይቅር ለማለት እምነትህ በቂ ስለ መሆኑ በምን ታረጋግጣለህ?
3. የምታገለግለው በግዴታ ነው ወይስ በውዴታ? ትእዛዛቱን ለመፈጸም ትሰለቻለህን ወይስ ከታዘዝኸው አብልጠህ በምስጋና እየተሞላህ ትሠራለህ?
4. በለምጻሞቹ ላይ ምን መልካም አርአያነት ይታያል (12-14)? ፈውስን መቼ ተቀበሉ?
5. ሳምራዊው ከታዘዘው ይልቅ ምን አደረገ (15-19ን ከቍ.10 ጋር አያይዝ)?
6.* ይህ ታሪክ ሰው ከኃጢአት ከሚድንበት መንገድ ጋር በምን ይመሳሰላል?

ቍ.6 የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት፤ 13፥18-19 ተመ.። የክርስቲያን ኃይል በእምነቱ ሳይሆን በሚታመንበት በእግዚአብሔር ነው።

ቍ.7-10 ይህ ምሳሌ የዓለማዊ ሰው የግዴታ አገልግሎት መንፈስን ያሳያል።

ቍ.11 ሉቃስ ትክክለኛውን መንፈስ ለማሳየት ከዚህ በፊት ወደ ተደረገው ተአምር ትረካ ይመለሳል።

ቍ.12 ለምጻሞች፤ የ5፥12ን ማስታወሻ ተመ.።

ሳምንት 17 ሐሙስ — ሉቃስ 17፥20-37

መግቢያ፤ የብሉይ ኪዳንን ትንቢት ያወቁት አይሁድ የእግዚአብሔርን መንግሥት መገለጥ ይጠባበቁ ነበር፤ ተስፋቸው ግን በዳዊት ዘመን እንደነበረው ምድራዊ ዓይነት መንግሥት ነበረ።

1. የእግዚአብሔር መንግሥት በክርስቶስ ጊዜ የት ተገኘ (ቍ.21)?
2. የእግዚአብሔር መንግሥት ወደፊት በምን አኳኋን ይገለጣል (22-30)?
3. አንድ ሰው «ክርስቶስ በዚህ ጊዜ ይገለጣል» ቢልህ ምን መልስ ይኖርሃል?
4. የሎጥ ሚስት የምን ዓይነት ሰው ምሳሌ ነበረች (31-37)?
5. የቍ.37ን ተረት «ወዴት ነው?» ከሚለው ጥያቄ ጋር አያይዝ።

6. የሕይወትህን ዓላማና ውጤት ከቍ.33 ጋር አነጻጽር።

ቍ,26 ኖኅ፤ ዘፍ.6፥11-22።

ቍ.28 ሎጥ፤ ዘፍ.19፥12-26።

ቍ.31 ይህ ማስጠንቀቂያ በማቴ.24፥17-18ና በማር.13፥15-16 ከኢየሩሳሌም መውደቅ በፊት የነበሩትን ቀኖች ያመለክታል፤ ይህም በ70 ዓ.ም ተፈጸመ። ማስጠንቀቂያው ደግሞ ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ተስማሚ ነው፥ ምክንያቱም ክርስቲያን ለጌታ መምጣት ዝግጁ ለመሆን ከዓለማዊ ሐሳብና ጉዳይ በፊት መንፈሳዊውን ማስቀደም አለበት፥ አለበለዚያ ግን ይጠፋል (32-33)።

ቍ.37 ሥጋ (በድን) ... አሞራዎች፤ መንፈሳዊ ግድፈትና ሞት ባለበት ሁሉ ፍርድ አይቀርም፤ የዘመኑ አባባል ይመስላል።

ሳምንት 17 ዓርብ ሉቃስ 18፥1-17

መግቢያ፤ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚያምን ሰው መምጣቱ የዘገየ ሲመስለው በምን አኳኋን መጸለይ እንደሚገባው የዛሬው አንቀጽ ያሳየናል።

1. ሀ)መበለቲቱ የእግዚአብሔርን ምርጦች፥ ለ)ዳኛው እግዚአብሔርን በምን ይመስላሉ (ቍ.1-8)?
2. እምነትህ ዘወትር ለመጸለይ ይገፋፋሃልን (1፡8)? ለምን?
3. የፈሪሳውያንን ስሕተት ዘርዝር (9፡11፡12፡14)።
4. በትክክለኛው መንገድ ራስህን ዝቅ ማድረግ እንዴት ትችላለህ(13)?
5. ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገባ የሚያስፈልገው በሕፃናት ዘንድ የሚገኘው ዓይነተኛ ጠባይ ምንድን ነው (13-15)?
6. ከዛሬው አንቀጽ ስለ ጸሎት የተማርከውን ዘርዝረህ በሕይወትህ አውለው።

ቍ.8 እምነትን ያገኛ ይሆንን? ፤ አማኞች ይገኛሉ (17፥34-36)፥ ግን እንደ መበለቲቱ በጸሎት የሚተጋ ክርስቲያን ይገኛ ይሆንን? ማለቱ ነው።

ቍ.12 ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፤ በአይሁድ ብዙ ጾም አልተመደበም፤ አንዳንዶች ሰኞና ሐሙስ ይጾሙ ነበር።

አሥራት፤ ከአንዳንድ ገቢ እንጂ ከሁሉ በሕግ አልታዘዘም።

ሳምንት 17 ቅዳሜ ሉቃስ 18፥18-30

1. አለቃው ስለ፥ ሀ)ኢየሱስ (ቍ.18-19)፥ ለ)ሕግ (20-21)፥ ሐ)ዘላለም ሕይወት (18-23) ያልተረዳው ምን ነበረ?
2. የዘላለምን ሕይወት እንዳያገኝ የከለከለው ምን ነበረ (22-23)?
3. ሰው ሀብቱን ከማምለክ እንዴት ሊድን ይችላል (23-27)?
4. ሰው ሁሉን ትቶ ክርስቶስን ቢከተል ምን ያገኛል (28-30)?
5. የአንተ «ሀብት» ምንድን ነው? ምድራዊውን ሀብት ትተሃል ወይስ በመተው ላይ ነህ? ምንን በማግኘት ላይ ትገኛለህ?

ቍ.18 ቸር (ደግ)፤ አይሁድ እግዚአብሔርን እንጂ መምህራቸውን ቸር (ደግ) አይሉም ነበር።

ቍ.26 እንግዲህ ማን ሊድን ይችላል? የ16፥14-15ን ማስታወሻ ተመ.።

ሳምንት 18 እሑድ — መዝሙር 17 (18)

መግቢያ፤ ይህን ታላቅ መዝሙር ለመረዳት የዳዊትን ሕይወት ታሪክ መገንዘብ ይረዳል (1ሳሙ.16-2ሳሙ.8)። ዳዊት የተባበረውን የእግዚአብሔር ሕዝብ የገዛ፥ የከበቡትን ሕዝቦች ያሸነፈና ስለ ዘሩ በታላቅ የተሰፋ ቃል የተባረከ ንጉሥ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ኃይልና ደግነት ከፍ ከፍ በማድረግ አምላኩን አመሰገነ።

1. እግዚአብሔር ዳዊትን ከምን አድኖት ነበር (ቍ.1-6፥16-19)?
2. በቍ.7-15 የሚገኘው ምሳሌ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይገልጣል?
3. እግዚአብሔር በጸሎተኛው የተደሰተበት ነገር ምንድን ነው (20-30)?
4. የእግዚአብሔር ኃይል በቍ.31-45 በምን ምሳሌዎች ተገልጦአል? ከሁሉ የሚያጽናናህ የትኛው ነው? ለምን?
5. በቍ.46-50 ከሚገኙት ሐረጐች በሕይወትህ የተፈጸሙት የትኞቹ ናቸው?

ቍ,10 ኪሩቤል፤ ዘፍ.3፥24ና ማስታወሻ ተመ.።

ሳምንት 18 ሰኞ — ሉቃስ 18፥31-43

1. ኢየሱስ በሕማማቱ ስለሚፈጸመው ምን ተጨማሪ ነገር ገለጠ (9፥21፥22፥44)?
2. የዕውሩን ሕይወት ሁኔታ ለመገመት ሞክር፤ ከዚህ በፊት ስለ ኢየሱስ ምን የሰማ ይመስልሃል?
3. ሰዎች ዕውሩን ለምን ገሠጹት (37-38)?
4. ኢየሱስ «ምን ላደርግልህ ትወዳለህ?» በማለት ዕውሩን ለምን ጠየቀ?
5. ከዚህ ታሪክ ስለ ኢየሱስ ባሕርይ ምን ትማራለህ? ይህም ምን ተስፋ ይሰጥሃል?
6. ከኢየሱስ በረከትን እንዳትቀበል፥ ሀ)እንቅፋት ሆኖብህ የነበረውን ነገር ታስተውላለህን? ፥ ለ)ተመሳሳይ እንቅፋት አሁን በሕይወትህ ውስጥ ይኖር ይሆን?

ቍ.31 ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፤ 9፥31፥51 ተመ.።

ቍ.38 የዳዊት ልጅ፤ ለመሲሕ የተሰጠ የማዕረግ ስም።

ሳምንት 18 ማክሰኞ — ሉቃስ 19፥1-10

1. ዘኬዎስ ምን ዓይነት ሰው ነበረ (ቍ.1-4፥8)?
2. ኢየሱስ ዘኬዎስን ሲፈልግ ልቡን እንዴት አገኘ?
3. አንተ የሰውን ልብ ለማግኘት ምን ታደርጋለህ?

4. ጽኪዎስ መዳኑን እንዴት ገለጠ? ከመዳንህ የተነሣ ምን ለውጥ በሕይወትህ ታያለህ?

5. ኢየሱስ ጽኪዎስን እንዴት አጽናናው (7፡9፡10)?

6. ሥጋዬን ስማቸውቶት ስትኖር የትኛውን ትመርጣለህ? ሀ)ደግ ወር ሆንትና ወደ እምነት ሰዎች ነውን? ወይስ፡ ለ)ወደ ሩጠፉትስ? ለምን?

ሮ.1-2 የሳሬሙኝ አለታ፣ የ3፡12ን ማነታወሻ ተመ.። ኢያሪኮ ከኢየሩሳሌምና ከሞርሳኮስ በስተ ምሥራቅ በአሥራት አገሮች መካከል የምገኘ መናኛ በመሆኑ ትልቁ የንግድ ማዕከል ነበረው። ጽኪዎስም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በመሰብሰብ ሀብቱን እንደጨመረ ነው።

ሮ.2 ሥራም ... ነጋዴዎችን፣ 5፡30፡7፡39፡15፡2።

ሮ.8 አራት እጥፍ እመልሳለሁ፣ ይህን በማለቱ ኃጢአቱን ተናዘና ትቶ በሕግ የመኖር ፈቃድን አሳየ (ዘጸ.22፡1፤2ሳሙ.12፡6)።

ቊ.9 የአብርሃም ልጅ፣ በሥጋዊ ረገድ ብቻ ሳይሆን በእምነት ጭምር ነው (ሮም 4፡12)።

ሰምንት 18 ረቡዕ — ሉቃስ 19፡11-28

መግቢያ፣ በዛሬው አንቀጽ የሚገኘው ምሳሌ ከ30 ዓመታት በፊት በሆነው ድርጊት ላይ የተመሠረተ ይመስላል። ታላቁ ሄሮድስ ከሞተ በኋላ በኑዛዜው መሠረት ልጁ አርኬላዎስ የንጉሥነት ማዕረግ ለመቀበል ወደ ሮም ሲሔድ፡ የአገሩ ሰዎች እንዳይሾም ለቄሣር መልእክተኞች ላኩበት፤ ግን አልተሳካላቸውም (ቊ.12፡14፡27፤ማቴ.2፡22)።

1. ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ለምን ተናገረ (11፡12፡28)?
2. ሠራተኞቹ የጌታቸውን መምጣት በምን ሁኔታና መንፈስ ጠበቁት (16፡18፡20፡21)?
3. ንጉሡ ደስታውንና ቊጣውን እንዴት አሳየ (17፡19፡22-27)?
4. አንተ የፍርድን ቀን በደስታ ወይስ በፍርሃት ትጠብቃለህ (2ቆሮ.5፡10)? ለምን?
5. አሁን እንዴት «ትነግዳለህ»?

ቊ.13 ምናን (መቶ ብር)፤ የሦስት ወር ደመወዝ ያህል።

ቊ.21 ጨካኝ ሰው መሆንህን፤ በመንፈስ የደከመ ሰው ብዙ ጊዜ እንደዚህ ያስባል (ዘፍ.3፡5)።

ቊ.27 ገደሉአቸው፤ በ70 ዓ.ም የተፈጸመውን የኢየሩሳሌምን መፍረስ ሊያመለክት ይችላል። ንጉሡን በተቃወሙት ላይ የደረሰው ፍርድ ከሰነፉ ሠራተኛ ይልቅ እጅግ ባሰባቸው።

አሪት ዘጸአት

አሪት ዘጸአት ማለት የመውጣት ሕግ ማለት ነው። መጽሐፉ የአሪት ዘፍጥረትን ታሪክ ይቀጥላል። እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከዘሩ ጋር ቃል ኪዳን

ገብቶ የከነዓንን ምድር እንደሚወርሱ ተስፋ ሰጥቶአቸው ነበር። በግብጽ የመገኘታቸው ሁኔታ ደግሞ ከ400 ዓመታት በፊት ለአብርሃም የተሰጠ የትንቢት ፍጻሜ ሆነ (ዘፍ. 15፥13)።

የያዕቆብ ቤተሰብ ወደ ግብጽ በወረደ ጊዜ የቤተሰቡ አባላት ቍጥር ሰባ ነበረ፤ በኋላ ግን ዝርያዎቻቸው በመብዛታቸው ለትልቅ ሕዝብነት በቅተዋል፥ ሆኖም አገር፥ ሕግ፥ አስተዳደርና ብሔራዊ ሃይማኖት አልነበራቸውም። በዚህ መጽሐፍ ነፃነትን ሲያገኙ፥ ሕግ ሲሰጣቸው፥ አስተዳደር ሲደራጅላቸው፥ ካህናት ሲለዩላቸውና ማምለኪያም ሲሠራላቸው እናያለን። ይህም ሁሉ የሆነላቸው እግዚአብሔር ባሰነሣላቸው በታላቁ መሪአቸው በሙሴ ነበረ።

ታሪኩን ስንከታተል ስለ እግዚአብሔር ስም፥ ባሕርይ፥ ሥልጣን፥ አለመለወጥ፥ የማዳን መንገድና ስለ ሕዝቡ ማኅበራዊ ኑሮ ደንብና አምልኮት እንማራለን።

መጽሐፉ ሙሴ ራሱ አንዳንድ አንቀጾችን እንደጻፈ ከመግለጡም በላይ (17፥14፤24፥4፤34፥27)፥ ኢያሱ የዘጸ. 20፥25ን ትእዛዝ ሲጠቅስ «የሙሴን ሕግ መጽሐፍ» (ኢያሱ 8፥31)፥ ደግሞም ጌታችን «በሙሴ መጽሐፍ በቍጥቋጦው ዘንድ የተጻፈውን አላነበባችሁምን?» (ማር. 12፥26) በማለታቸው፥ ጠቅላላው መጽሐፍ በሙሴ አማካይነት መገኘቱ ከጥንት የመጣ አመለካከት እንደሆነ ያሳያል። ከዚያ ወዲህ ግን አንዳንዶቹ መጽሐፉ ከሙሴ ዘመን በኋላ እንደተዘጋጀ ይከራከሩበታል። «የአሪት ደራሲ»ን በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ተመልከት።

ሳምንት 18 ሐሙስ — አሪት ዘጸአት 1

1. ዮሴፍ ከሞተ በኋላ የግብጽ መንግሥት ስለ እስራኤላውያን የነበረውን አስተያየት ለምን ለወጠ (7-10፥12)?
2. ሕዝቡን ለማድከም ምን ዓይነት ምስት እርምጃዎችን መሰደ (11፥13፥14፥16)? ይህ ሁሉ ሳይሆን ሲቀር በመጨረሻ የወሰደው እርምጃ ምን ነበረ (22)?
3. ስለ ሰው ሕይወት የግብጻውያን አመለካከት እንዴት ነበረ?
4. የእስራኤል ሕዝብ ምኞት በዚያ ዘመን ምን እንደነበረ ገምት?
5. ለእግዚአብሔርና ለባለሥልጣናት በመታዘዝ መካከል ግጭት ሲፈጠር ከአዋላጆቹ ታሪክ ምን መጽናኛ ታገኛለህ?

ቍ.5 ሰባ ነፍሶች፤ በሐ.ሥ.7፥14 የተጠቀሱት 75 ሰዎች የኤፍሬምንና የምናሴን አምስት ልጆች ሊያጠቃልሉ ይችላሉ።

ቍ.8 አዲስ ንጉሥ፤ ምናልባት አዲስ ሥርወ መንግሥት ከሌላ ወገን ሆኖ አዲስ ፖለቲካ ተከትሎ ይሆናል።

ሳምንት 18 ዓርብ — <u>አሪት ዘጸአት 2</u>

1. የሙሴ እናት፥ ሀ) ልጅዋን ለምስት ወር እንዴት ጠበቀች (1-2)? ለ) በኋላም ልጅዋን በግሳደግ ደመወዝን ለመቀበል እንዴት ቻለች (3-9)?

2. ሙሴ የጉባኤን ትምህርት ሁሉ ለመግር እንዴት ቻለ (10)?

3. የአደግህበት አካባቢና ሁኔታ ለሕይወትህ ምን አስተዋጽኦ አደረገልህ? ለዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን ታመሰግናለህን?

4. እግዚአብሔር፥ ሀ) ሙሴ ጉባዔዊውን መግደሉን በዘላለም ፅድቁ እንዴት አጠቃለለው (11-15፡23-25)፥ ለ) ለሙሴስ ስፍራውን እንዴት አዘጋጀ (16-22)?

5.* የሙሴ እናትና የሙሴ እምት በዚህ ምዕራፍ እንዴት ይገለጣሉ (ዕብ.11፥24፡26)?

ቍ.1 ከሉዊ መጣ፤ በዚህ ጊዜ የተረገሙ መጣ ነበረ (ዘፍ.49፥5-7)፥ የከሃት አገልግሉት የተሰጣቸው በኋላ ነበረ (ዘጸ.32፥25-29)።

ቍ.4 እኅቱ፤ ማርያም (ሚርያም፤ 15፥20)።

ቍ.11 ሙሴ ጎበዝ በሆነ ጊዜ፤ በሐ.ሥ. 7፥22፡23 መሠረት የጉባዔውያንን ጥበብ ሁሉ ተምሮ ዕድሜው 40 ዓመት ነበረ። በጉባኤ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ድርሰት፥ሕግ፥አስተዳደር፥ሥርዓትና የሕገጻ አሠራር ይሰጡ ነበር። ሙሴ ይህን ሁሉ ሲያጠናና በተችን ለአርባ ዓመታት ሲያስተራ እግዚአብሔር በሕይወቱ ለታላቅ ሥራ ያዘጋጀው ነበር (7፥7 እና ግለታመሻ ተመ.)።

ቍ.15 ምድያም፤ አብርሃም ከኬጡራ የመለደው የምድያማውያን አባትና ከጉባኤ በስተ ምሥራት ያለ የአገር ስም (ዘፍ. 25፥1፡2)።

ሳምንት 18 ቅዳሜ

<u>ኦሪት ዘጸአት 3</u>

1. ሙሴ አርባ ዓመታት በምድረ በዳ በተችን ከጠበቀ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኘው ጊዜ እንዴት ደረሰ (ቍ.1-4)?

2. ሙሴ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና ማንነት ምን ተረዳ (5-6)?

3. የእስራኤል ሕዝብ ጩኸት፥ የእግዚአብሔር ፅድድና የሙሴ ተልእኮ እንዴት ተጣመሙ (7-10)?

4. እግዚአብሔር ለሁለቱ የሙሴ ጥያቄዎች (11፡13) መልስ ሲሰጥ ምን ተስፋ ሰጠው (12፡14-22)?

5. እግዚአብሔር ለእንድ ሥራ ሲመራህ ምን ያህል ግውት ያስፈልግሃል?

6.* ከቍ.12-22 ስለ እግዚአብሔር ማንነት፥ ባሕርይና ዕቅድ ምን ትግራለህ? ይህ ለሕይወትህ ምን ለውጥ ያመጣል?

<u>ቍ.1 ዮቶር (የትር)</u>፤ ከሙሴ ጋብቻ በፊት ራጉኤል ይባል ነበር (2፥18)።

ኮራብ፤ በሲና ምድረ በዳ የሚኖ ተራራ፤ ብዙ ጊዜ ሲና ይባላል (19፥2)።

ቍ.2 የእግዚአብሔር መልአክ፤ እግዚአብሔር በሚታይ መልክ ተገለጠ (ዘፍ.18፥1፤32፥24-30)።

ቍ.5 የተቀደሰች መሬት ናት፤ እግዚአብሔር በዚያ ስለ ተገኘና ራሱን ስለ ገለጠ።

ቍ.13 ስሙስ ማን ነው? ፤ ከዚህ በፊት እግዚአብሔር ማንነቱንና ባሕርዩን በልዩ ልዩ ስሞች ገልጾ ነበር (ዘፍ. 17፥1፤35፥1)።

ቍ.14 «ያለና የሚኖር»(ያለውና የምኖር)፤ የእግዚአብሔር ስም የ«ያህዌ» ትርጉም።

<u>መግቢያ፤</u> እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን አራሱን የገለጠበት ከዚህ መዝሙር ሌላ የላቀ አይገኝም። በዚህ መዝሙር፥ (ሀ) እግዚአብሔር የሰምች ሁሉ ፈጣሪ እንደሆነ (ቍ.1-6)፥ (ለ) ለቤተ እስራኤል ሕግ እንደሰጠ (ቍ.7-11)፥ (ሐ) ለማንኛውም ኃጢአተኛ አዳኝ እንደሆነም (ቍ.12-14) ተገልጿል።

1. ሥነ ፍጥረት ስለ እግዚአብሔር የሚገልጠው ምንድን ነው (ቍ.1-6)?
2. ዳዊት የእግዚአብሔርን ፈቃድ በስድስት ቃላት ሲያብራራ የእያንዳንዱ ቃል ዓላማ ምንድን ነው (7-9)?
3. የእግዚአብሔር ቃል በመሠረቱ ምን ይመራል (10-11)?
4. ዳዊት የእግዚአብሔርን ቃል ካስተዋለ በኋላ መሰናከል እንዳይሆኑበት የጸለየባቸው ሁለቱ ኃጢአት ምን ምን ናቸው (12-14)?
5. የእግዚአብሔርን ፍጥረትና የእግዚአብሔርን ቃል ስትመረምር የሚሰማህን ዝትተኝነትና ጉድለት ግለጽ።
6. ስለዚህ ምን ማድረግ ይገባሃል? በተለይ ቍ.14 እንዴት ይጠቅምሃል?

ቍ.5 ፀሐይ፤ የእግዚአብሔርን ክብር፥ ባሕርይና ሥራ ያሳየባል፤ ይህንም በደብዳቤ ለማብራራት የፀሐይ መውጣትና አኳሐድ በመሬራና በአርበኛ(ወይም በጅጭ) ተመሰሉ ይታያል።

ቍ.7 ሕግ፤ ሲባል የተገለጠ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ነው።

<u>ምስክር፤</u> ስእግዚአብሔር በራሱ የተረጋገጠ እውነተኛ ነገር በተለይ ቃል ኪዳን ውስጥ ስእግዚአብሔር የተሰጠ ትእዛዝና ተስፋ ነው።ዘጸ.25፥22።

<u>ቍ.8 ሥርዓት...ትእዛዝ፤</u> እነዚህ ቃላት እግዚአብሔር ለሰው እንደ ሥልጣኑ በተመሰኩ ነገሮች ላይ በተጭ ፈቃዱን እንደገለጠ ያሳያሉ።

ሳምንት 19 ሰኞ ኦሪት ዘጸአት 4

1. እግዚአብሔር ለምስተኛው የሙሴ ጥያቄ ምን መልስ ሰጠ? የምስቱ ምልክቶች ዓላማ ምን ነበረ (1-9)?
2. የመጀመሪያዎቹ የሙሴ ጥያቄዎች ተገቢ ቢሆኑም፥ አራተኛው ጥያቄ ተገቢ ነበርን (ቍ.10ን ከ3፥12 ጋር አነጻጽር)? እግዚአብሔር ግን እንዴት አደሩራረው (11፥12፥14-17)?
3. ከእነዚህ አራት ጥያቄዎች በስተኋላ ሙሴ ያመነታባትን ምክንያት ለመገለጥ ሞክር (13)። አንተ የምታመነታበት ምክንያት አለህን?
4. ሙሴ የመታዘዝን የመጀመሪያ እርምጃ ሲወስድ እግዚአብሔር እንዴት አጽናናው (18-23)?
5. በሙሴ ዘንድ ገና ያልተፈጸመ ነገር ምን ነበረ (24-26)? ለዚህ ሲታዘዝ እግዚአብሔር እንዴት አጽናናው (27-31)?
6. እግዚአብሔር በትርብ ጊዜ ተቈጣህን (14፥24)? ለምን? እየታዘዝህ ስትሬመድ በየጊዜው የእግዚአብሔርን መጽናኛ ተቀብለሃልን?

ቍ.10 እረ ትብ ሰው አይደለሁም (የመናገር ችሎታ የለኝም)፤ ኤር.1፥6 ተመ.።

ቍ.19 ሞተዋልና፤ ግቴ.2፥20 ተመ.።

ቍ.21 ልቡን አጸናዋለሁ (ኽልከኛ ስለማደርገው)፤ በአሪት ዘጸአት እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ እንዳጸና ዘጠኝ ጊዜ ሲጻፍ፥እንዲሁም ደግሞ ፈርዖን ራሱ ልቡን እንዳደነደነ ዘጠኝ ጊዜ ተጽፎ እናገኛለን (ለምሳሌ 8፥15፡32)። ለአሪት አዘጋጅ ግን በሁለቱ ሐሳቦች መካከል ምንም ግጭት አልነበረም። እግዚአብሔር የበጎ ድርጊት ምንጭ ነው፥ ያለ እርሱ ምንም አይሆንምና እግዚአብሔር ሰው እንደ ጠባዩ እንዲኖር ኃይልን ይሰጠዋል፥ሰውም ለሚያደርገው ሁሉ ተጠያቂ ነው። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሰውን ሳይገታ እንደ ክፋቱ ሁሉ የፈለገውን እንዲሠራ ይተወዋል (ሮም 1፥24፡26፡28)፤ ይህ ሲሆን ግን በፅትዱ ውስጥና ለራሱ ክብር ይሆናል (ሮም 9፥17-23)።

ቍ. 24 ሊገድለው ፈለገ፤ ሙሴ ልጁን ስላልገረዘ (25-26፤ ዘፍ.17፥9-14)።

ሳምንት 19 ማክሰኞ — አሪት ዘጸአት 5

1. ሙሴና አሮን ከፈርዖን ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገናኙ ምንን ለመኑ (ቍ.1-3)?
2. ፈርዖን ልመናቸውን በምን አኳኋን ተረጐመ (4፡5፡8፡9)? ምን አደረገ (6፡7)? ለምን (2)?
3. ፈርዖን አቤቱታቸውን ባልተቀበለ ጊዜ የእስራኤል አለቆች ሙሴንና አሮንን በምን መንፈስ ተናገሩ (21)?
4. ሙሴ ምን አደረገ (22-23)?
5. ሥራህ ሳይሳካልህ ሲቀር ወይም ሰዎች በምክንያት ሲወቅሱህ ምን ታደርጋለህ?

ቍ.1 ጉበጻውያን እንስሳትን በተለይም ከብቶችን እንደተቀደሱ ፍጥረታት በመቍጠራቸው እስራኤላውያን በጉበጽ እንስሳት ለመሠዋት አይችሉም ነበር (8፥26)።

ቍ.2 እግዚአብሔርን አሳውቅም፤ እንደ ፈርዖን አስተሳሰብ እያንዳንዱ አምላክ የራሱ የተወሰነ ሥልጣንና ኃይል ነበረው።

ቍ.6 አስጣሪዎች ጨማምንተዝም (ጉበጻውያን አሠሪዎችና የእስራኤላውያን ሠራተኞች አለቆች)።

ሳምንት 19 ረቡዕ — አሪት ዘጸአት 6

1. እግዚአብሔር ለሙሴ መራራ ጩኸት መልስ ሲሰጥ ደጋግሞ የገለጸው ሐረግ ምንድን ነው (ቍ.3፡6፡8፡29 ደግሞም 7)?
2. ለአብርሃም እግዚአብሔር ራሱን በምን አኳኋን ገልጦ ነበር (3)?
3. አሁን «እግዚአብሔር» (ያህዌ) በተሰኘው ስም ማንነቱንና ባሕርዩን በምን ሰባት መንገድ ገለጠ (3፡6-8)?
4. እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ተአምራትና በረከት በአሁኑ ሰዓት ለእንተ ከሚያደርገው ጋር አነጻጽር።
5. ሙሴ ወገኖቹ ሳይሰሙት ሲቀሩና እግዚአብሔር «ለፈርዖን ንገር» ብሎ በድጋሚ ባዘዘው ጊዜ ምን መልስ ሰጠ (9-13፡28-30)?

6. ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ስትገኝ የድሮ ምክንያትህን ሁሉ ትደግማለህ ወይስ መፍትሔን ትፈልጋለህ (ዮሃ. 12፡30፤ 14፥12)?

ቁ.3 ሁሉን እንደሚችል አምላክ፤ የ«ኤልሻዳይ» ትርጉም(ዘፍ. 17፥1)።

ስሜ እግዚአብሔር (ያህዌ) አልታወቀላቸውም ነበር፤ ከአባቶቹ አንዳንዶች በዚህ ስም ይጠቀሙ ይሆናል (ዘፍ.4፥26)፥ ሆኖም እንደ መሪታዊ ትርጉሙ እግዚአብሔርን አላወቁም። አሁን እግዚአብሔር እስራኤልን ከባርነት ነፃ በማውጣት የኃያልነቱን ባሕርይ ይገልጣል። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ይህን ስም እንዳልታወቀ አድርጎ አሁን ለሙሴ ያብራራል።

ቁ.13-25 የሙሴና የአርን ስፍራ በእስራኤል መካከል የት እንደነበረ ለመገለጥ ከሌዊ ታላቅ የነበሩት የሮቤልና የስምዖን ዝርያዎች ተጠቅሰዋል፥ በኋላም የያዕቆብ ምስተኛ ልጅ የሌዊ የትውልድ ሐረግ ተጽፎአል።

ሳምንት 19 ሐሙስ — አሪት ዘጸአት 7

1. እግዚአብሔር ለሙሴ መራራ ጥያቄ (6፥30) መልስ ሲሰጥ በምን ላይ አተኩረ (ቁ. 1-5)?
2. የአርንንና የግብጻውያንን አስማተኞች ምልክቶች አነጻጽር (8-13)?
3. ውኃው ወደ ደም መለወጡ፥ ሀ) በእስራኤላውያን፥ ለ) በግብጻውያን አስተሳሰብ ላይ ምን ለውጥ ያመጣ ይመስልሃል (14-24)?
4. የፈርዖንን አለመታዘዝ፥ ሀ) የእግዚአብሔርን ማንነት ካለማወቁና፥ ለ) ስለ ራሱ ከነበረው አመለካከት ጋር አስተያይ።
5. ስለ እግዚአብሔር ያለህ እውቀት ምግባርህን ሁሉ ምን ያህል ይመራዋል?

ቁ.7 የሰማንያ ዓመት ሰው ነበረ፤ የሙሴ ሕይወት ታሪክ በሦስት ደረጃዎች ሊከፈል ይቻላል :- 1.አርባ ዓመት በፈርዖን ቤት እያደገ የግብጽን ጥበብ መማሩ፥ 2.አርባ ዓመት የአማቱን ዕንች እየጠበቀ በእግዚአብሔር መዘጋጀቱና 3.አርባ ዓመት የእግዚአብሔርን ሕዝብ እየመራ የእግዚአብሔርን ኃይል ማሳየቱ (ዘዳ.34፥7፤ሐ.ሥ.7፥23፡30)።

ቁ.17 ግብጻውያን የአባይን ወንዝ ያመልኩ ነበር።

ቁ.22 የግብጽም ጠንቋዮች በአስማታቸው እንዲሁ አደረጉ፤ በአሪት ዘጸአት ውስጥ ከሚገኙት መቅሠፍቶች አንዳንዶቹ በተፈጥሮ ሁኔታ እንደተከሠቱ የግብጽ ጠቢባን መድረሳቸውን ለማስተዋል የሚገምቱ አሉ። ለምሳሌ፥ ያውኃ ወደ ደም መለወጡ አባይ ከጎኛም ብዙ ቀይ አፈር ይዞ ወደ ግብጽ ሲወርድ ለግብጽ አባይ ቀይ መልክ ዛሬ እንደሚሰጠው ሁሉ ይሆናል። ሆኖም ከፍ ባለ ሁኔታና ልክ ሙሴ በተናገረበት ወቅት በመሆኑ መቅሠፍቱ ከእግዚአብሔር እንደመጣ ግልጥ ነበረ።

ሳምንት 19 ዓርብ — አሪት ዘጸአት 8

1. ፈርዖን ጓጉንቸሮችን ለማራቅ አስማተኞችን ትቶ ሙሴን ለምን ጠየቀ (7-8)?
2. ሙሴ ወዲያው ለምን አልጸለየም (9-15)?

3. በትግል መቅሠፍት ምክንያት አስግተኞቹ ለፈርዖን ምን ምክር ሰጡት? ለምን (18-19)?

4. በዝንብ መንጋ መቅሠፍት ምን አዲስ ነገር ተገኘ (21-22)? የእስራኤል ሕዝብ ይሆን ሲያይ ምን እንደተሰማው ገምት።

5. ፈርዖን ከሙሴ ጋር ለመከራከር እንዴት ሞከረ? ምን ሆነ (25-32)?

6. አንተ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ባልፈለግህበት ጊዜ ምን አደረግህ? ምን ሆነ?

ቍ.2 ጓጕንቸሮች፤ ሴቶችን ለመውለድ የምትረዳ የጎበጠ አምላክ ምስል ጓጕንቸር ነበረች።

ቍ.18 አልተሳካላቸውም፤ ከዚህ በኋላ የጎበጠ ጠቢባን ከሙሴ ጋር መወዳደርን ተዉ።

ሳምንት 19 ቅዳሜ — አሪት ዘጸአት 9

1. በእነዚህ ምስት መቅሠፍቶች ምን ጉዳት ደረሰ (ቍ.6፡10፡11፡20-26፡31)?

2. በእነዚህ መቅሠፍቶች ሁሉ የእግዚአብሔር ጣዖራ ዓላማ ምን ነበረ (13-16)?

3. ፈርዖን «በዚህ ጊዜ በደልሁ» በማለቱ ንስሓ ገባ ወይስ በመቅሠፍቶቹ ጉዳት ምክንያት ጸጸቱን ብቻ ገለጠ (27-30፡34፡35)?

4. በአንተ ሕይወት ውስጥ ስለ በደልህ ንስሓ ወይም ጸጸት እንዳለ በምን ሁኔታ ይገለጣል?

5.* ከዚህ ምዕራፍ ስለ ሙሴ ጠባይ ምን ትማራለህ?

ቍ.6 የጎበጽም ኩበት ሁሉ ሞተ፤ ይህ በበረት ውስጥ የነበሩትን ላይሆን በሜዳ ላይ የነበሩትን የሚያመለክት ይመስላል (19-21)።

ቍ.12 እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ አጸና፤ የ4፡21ን ማስታወሻ ተመ.።

ቍ.16 ሮም 9፡16-18 ተመ.።

ሳምንት 20 እሑድ — መዝሙር 19(20)

1. ይህ መዝሙር የተገኘው በምን ዓይነት ሁኔታ ነበረ (ቍ.1-5)?

2. የንጉሡ ምኞት ምን ነበር? ምኞቱንስ እንዴት ገለጠ?

3. በእግዚአብሔር፥በሕዝብና በንጉሥ መካከል የነበረው ግንኙነት እንዴት ነበረ (6-9)?

4. ክርስቶስ ንጉሣችን ሆኖ በአሁኑ ሰዓት ምኞቱ እንዴት በመፈጸም ላይ እንዳለ አሰላስል።

5. የእስራኤልንና የጠላቶቻቸውን ተስፋና ውጤት አነጻጽር (7-8)።

6. ችግር ሲያጋጥምህ ምን ታደርጋለህ? ተስፋህስ ምንድን ነው?

ቍ.6 የቀባውን (መርጦ ለቀባው ንጉሥ)፤ ንጉሥ፥ ነቢይ ወይም ካህን ለተለየ አገልግሎት በእግዚአብሔር ሲመረጥ በዘይት ይቀባ ነበር። ጠቅላላው የሕዝብ አንድነት፥ተስፋ፥ ባህልና መልክ በንጉሥ መንጸባረት ነበረበትና በእነዚህ ሁሉ ከንጉሥ

መልካም አርአያ ይጠበቅ ነበር። ይህም ከሰው አቅም በላይ በመሆኑ በክርስቶስ ብቻ ተፈጸመ።

ቍ.7 በመረገላ...በፈረስ፤ መዝሙረኛው ዛሬ ቢጽፍ ኖሮ በከባድ የጦር መሣሪያዎች ግለትም በታንክ፥ በአይሮፕላንና በመሳሰሉት ሐሳቡን ይገልጥ ነበር።

<u>ሳምንት 20 ሰኞ</u> አሪት ዘጸአት 10

1. ሙሴ ስለ አንበጣ መንጋ ፈርዖንን ሲያስጠነቅቅ መኳንንቱ ምን አሉት (ቍ.1-7)?
2. ሙሴ የፈርዖንን ውሳኔ ሲሰማ ምን አለ (8-11)?
3. እግዚአብሔር ምሕረቱን ካሳየው በኋላ ፈርዖን ሕዝቡን ለምን አልለቀቀም (1፥2፥12-20)?
4. የጨለማ መቅሠፍት ሲመጣ ፈርዖን ስለ እስራኤል ሕዝብ መለቀቅ ምን ለመወሰን ሞከረ (21-24)?
5. ፈርዖን በሙሴ ላይ ተቈጥቶ እንዴት አሰናበተው (25-29)?
6. ለእግዚአብሔር ስትታዘዝ ከትእዛዙ ውስጥ አንዳንዱን ነገር ችላ ትላለህ ወይስ በሙሉ ልብ ትታዘዛለህ?

ቍ.4 አንበጣዎች፤ በምድረ በዳ አጠገብ ለሚኖሩ ሕዝቦች ከባድና አስፈሪ መቅሠፍቶች ስለ ነበሩ፥ የአምላክ ፍርድ ምሳሌ ሆኑ (ኢዩ.1፥1-7፤ አሞጽ 7፥1-3)።

<u>ቍ.21 ጽኑ ጨለማ</u>፤ እንደ ምስተኛውና እንደ ስድስተኛው መቅሠፍት ሁሉ ከዚህ መቅሠፍት በፊት ማስጠንቀቂያ አልተሰጠም። ጨለማው በአውሎ ነፋስ ከተነሣው አሸዋ የተፈጠረ ይሆናል። ጨለማውም የግብጽ የፀሐይ አምልኮ ከንቱ እንደነበረ ገለጠ።

<u>ሳምንት 20 ማክሰኞ</u> አሪት ዘጸአት 11፥1-10፤ 12፥1-20

1. እግዚአብሔር ስለ አሥረኛው መቅሠፍት አስቀድሞ ምን ገለጠ (11፥1-10)?
2. እስራኤላውያን ከመቅሠፍቱ ለመዳን ምን እንዲያደርጉ ታዘዙ (12፥1-13)?
3. የፋሲካ ዓመታዊ መታሰቢያ በምን አኳኋን እንዲከበር ታዘዘ (12፥2 ፥14-20)?
4. እግዚአብሔር ለአንተ ያደረገውን ታላቅ ተአምር እንዴት ታከብራለህ?
5.* የፋሲካን በግ ከክርስቶስ ሞት ጋር አነጻጽር (1ቆሮ.5፥6-8፤ 1ጴጥ.1፥18-19)።
6.* የፋሲካን ዓመታዊ መታሰቢያ ከቅዱስ ቍርባን ጋር አነጻጽር (ሉቃ.22፥14-20፤ 1ቆሮ.11፥23-26)።

11፥9፡10 እነዚህ ጥቅሶች የፈረዖንን አልኾነት በአጭሩ ይገልጣሉ።

12፥7 ከደሙም ወሰደ፤ ፋሲካ እንደ ኃጢአት መሥዋዕት አልተደነገገም፥ ነገር ግን ሥርዓቱ ሰውን ከእግዚአብሔር ፍርድ የሚሸፍን መሥዋዕትን ይመስላል።

12፥11 ፋሲካ፤ ቃሉ በዕብራይስጥ «አለፈ» ማለት ነው፤ እዚህ ላይም «አይተ ሳይፈርድ ተው» ተብሎ ሊተረጐም ይቻላል (13)።

12፥15 ቂጣ እንጀራ (እርሾ ያልነካውና ፈጽሞ ያልቦካ ቂጣ)፤ ቂጣው የእስራኤል ሕዝብ በችኮላ መውጣቱን ያመለክታል፤ ሊጡ እስኪቦካ ድረስ በቂ ጊዜ አልነበረምና(12፥39)።

ሳምንት 20 ረቡዕ — አሪት ዘጸአት 12፥21-51፤ 13፥1-16



1. ስለ ፋሲካ ሥርዓት ምን ተጨማሪ ትእዛዝ ተሰጠ (12፥21-28፤ 13፥1-7)? ለምን (13፥8-10)?
2. በፋሲካ ሌሊት የፈርዖን አካሔድ ምን ያህል ተለወጠ (12፥29-32)?
3. እስራኤላውያን ከግብጽ በምን አኳኋን ወጡ (12፥33-42፤ 3፥22)?
4. አንድ እንግዳ በፋሲካ በዓል እንዴት መሳተፍ ይችል ነበር (12፥43-51)?
5. የበኵር ሥርዓት ምክንያት ምንድን ነው (13፥1፡2፡11-16)?
6. * ከማናቸውም ባርነት ነፃ መውጣት እንዴት ትችላለህ (13፥3፡14፡16፤ ሉቃ. 11፥21 ፡22፤ ኤፌ. 1፥18-20)?

13፥13 ትዋጀዋለህ፤ ከሰውም ሆነ ከእንስሳ በመጀመሪያ የተወለደው እንደ እግዚአብሔር ልዩ ንኽብ ይቈጠር ነበርና (2)፥ ንጹሀ እንስሳ ይሠዋ፥ ርኩስ እንስሳ ይተካ ወይም ይገደል፥ እንዲሁም ለሰው ቤዛ ይሰጥ ነበር (ዘኍ. 3፥39-51)።

ሳምንት 20 ሐሙስ — አሪት ዘጸአት 13፥17-22፤ 14፥1-31

1. ስለ እግዚአብሔር መሪነት ከ13፥17-22 ምን ትማራለህ?
2. እስራኤላውያን በግብጻውያንና በባሕሩ መካከል ሲሆኑ በምን አኳኋን አንጐራጐሩ (14፥10-12)?

3. እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን በጎ ነገር ዘርዝር (14፥15-27)። ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር በማን ተከበረ (18፡31)?

4. ሙሴ በዚህ ታሪክ እምነቱን እንዴት ገለጠ (13-15፡21፡27)? ምንስ ሆነለት (31)?

5. በሕይወትህ የእግዚአብሔር ሥራ ውጤት (ተአምር) ምንድን ነው?

6.* ከዚህ ታሪክ ስለ፥ ሀ)እምነት፥ ለ)መሪነት ምን ትማራለህ (ዕብ.11፥29፤1ቆሮ.10፥2)?

13፥17 በፍልስጥኤማውያን ምድር መንገድ፤ በዚህ መንገድ የጎበጽ ሮር ሰፈር ይሻላ ነበር።

13፥18 በኤርትራ ባሕር (ቀይ ባሕር)፤ በዕብራይስጥ ቃሉ «የሸምበቆ ባሕር» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል።

14፥2 ተመልሰው በሚገዶልና በባሕር መካከል፤ ሚገዶልና ሌሎች ቦታዎች የት እንደነበሩ አናውቅም፤ አንዳንድ ሊቃውንት እስራኤላውያን ወደ ምሥራቅ ከተጓዙ በኋላ ወደ ሰሜን ተመልሰው በቀይ ባሕርና በታላቁ ባሕር መካከል ብዙ ሸምበቆ ባለበት ሐይቅ በስተምዕራብ እንደሰፈሩ ያስባሉ (ካርታ ተመ.)።

14፥5 ሕዝቡም እንደ ኩበለሉ፤ እስራኤላውያን ለመሠዋት ብቻ ሳይሆን ከጎበጽ ምድር ለማምለጥ እንደወጡ ፈርዖን አውን ተረዳ።

<u>ሳምንት 20 ዓርብ</u> ኦሪት ዘጸአት 15፥1-21

<u>መገቢያ</u>፤ ይህ መዝሙር እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ያደርጋል (ቍ.11)። የመጀመሪያዎቹ አራቱ ስንኞች (1-5፤6-8፤ 9-10፤11-12) የእስራኤልን መዳን ሲያመለክቱ፥ የመጨረሻው ወደ ከነዓን መድረስና ቅድስቲቱን አገር ስለ መያዝ ይተነብያል፤ ይህም በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል የተረጋገጠና የግይቀር በመሆኑ እንደተፈጸመ ተቈጥሮ በክይ አነጋገር በጎላሬ ጊዜ ተገልጦአል።

1. በዚህ መዝሙር ሙሴ፥ሀ) ከእግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ፥ ለ) ከእግዚአብሔር ሥራ ያተኩረበትን ዘርዝር (ቍ.1-12)።

2. ሙሴ የእግዚአብሔርን ባሕርይና ሥራ በመመርመር ለወደፊቱ ምን ተስፋ አገኘ (13-18)?

3. አንተ በእግዚአብሔር ባሕርይና ሥራ ተስፋህንና ዕቅድህን ሁሉ እንዴት ትመሠርታለህ?

4. የግርያም (የሚርያም) አገልግሎት ምን ነበረ (20-21)? ይህ ለዛሬ ሴቶች ምን አርአያነት አለው?

5.* እግዚአብሔርን የሚያመሰግን መዝሙር ወይም ግጥም ድረስ (ጻፍ) ወይም መርጠህ ዘምር።

ቍ.11 በአማልክት መካከል፤ እግዚአብሔር የጎበጹውያንን «አማልክት»ና አምላኪዎቹን ሁሉ አሸንፎ ነበር፤ ብሉይ ኪዳን ለእነዚህ አማልክት መሠረት እንደሌለ ይገልጣል (ኢሳ.45፥5፡6)።

ቍ.14፡15 ፍልስጥኤም...ኤዶም...ሞአብ...ከነዓን፤ የእስራኤልን ሕዝብ ጉዞ ቅደም ተከተል ያሳያል።

<u>ቍ.20 ነቢይቱ</u>፤ ዘኍ.12፥2ና ጠቅላላውን ምዕራፍ ተመ.።

ሳምንት 20 ቅዳሜ — ኦሪት ዘጸአት 15፥22-27፤ 16፥1-36

መግቢያ፤ እስራኤላውያን ከግብጽ ሲወጡ በፋሲካ ሌሊት በመዳናቸውና ቀይ ባሕርን በመሻገራቸው በሁለቱ ታላላቅ ድርጊቶች ተሳታፊዎች ነበሩ። እነዚህ ሁለት ተአምራት ተደጋግመው በእስራኤል ታሪክና መዝሙር ውስጥ ይገኛሉ። አሁን ግን ለእግዚአብሔር መታዘዝ ምን እንደሆነ መማር ነበረባቸው።

1. ሕዝቡ ለምንና በማን ላይ አጉረመረሙ (15፥22-24፤ 16፥1-3፡7)? ምን ማለት ነበረባቸው?
2. አንተ የምታጉረመርመው በምን ምክንያት ነው? በማን ላይ ነው? ማጉረምረምህስ ስለ እምነትህ ምን ያሳያል?
3. ሕዝቡ በሙሴ ላይ ሲያጉረመርም ሙሴ ምን አደረገ (15፥25፤ 16፥8፡9)?
4. እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ በምን አኳኋን ሰጣቸው (15፥25፡27፤ 16፥13-15፡35)?
5. እግዚአብሔር ስለ ዕለት ሥራና ስለ ሰንበት ዕረፍት እንዴት አስተማራቸው (16፥16-30)?
6.* እግዚአብሔር ለሚወዳቸው ጥምን፥ረሃብን፥ብስጭትን ለምን ይሰጣል? (15፥26፤ 16፥23፡28፡ 29፤ዘዳ.8፥2፡16፤ 1ጴጥ.1፥6 ፡7)?

16፥31 መና፤ በዕብራይስጥ «ይህ ምንድን ነው?» እንደ ማለት ነው (15)።

16፥33 ኀምር (ሁለት ሊትር)።

ሳምንት 21 እሑድ — መዝሙር 20(21)

መግቢያ፤ መዝ.20(21)፥2ን ከመዝ.19(20)፥4 ጋር ስናነጻጽር ጥንድ የሆኑ ይመስላል፥ ይኸውም የመጀመሪያው መዝሙር ልመና ሲሆን ሁለተኛው የጸሎት መልስ ነው። በመዝ.19(20) የሕዝቡ ጸሎት በንጉሡ ጸሎት ላይ እንደ ተጨመረ ሁሉ፥በመዝ.20(21) የሕዝቡ ምስጋና የንጉሡን ምስጋና ተከትሏል።

1. ንጉሡ ዳዊት ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበለውን በረከት ዘርዝር (ቍ.1-6)።
2. ዳዊት የደረሰበትን ችግር እንዴት በድል ተወጣው (7)?
3. የቀደመው ሕዝብ የድል ታሪክ ዳዊትን እንዴት አጸናናው (8-12)?
4. የንጉሡ ድል ማግኘት እግዚአብሔርን እንዴት ያስከብራል (13)?
5. በሕይወትህ፥ ሀ)የጸሎትህን መልስ ስትቀበል፥ ለ)በችግር ጊዜ አሸናፊ ስትሆን ምን ታደርጋለህ?

ሳምንት 21 ሰኞ — ኦሪት ዘጸአት 17

መግቢያ፤ ልዩ ልዩ ችግር በእስራኤላውያን ላይ እየደረሰ መጣ፤ እያንዳንዱንም ችግር ግለፋቸው ለሚቀጥለው ፈተና ያዘጋጃቸው ነበር።

1. 17፥1-7ን ከ15፥22-25 እና ከ16፥1-8 ጋር አነጻጽር። ምሬታቸው እንዳደገ በምን ይታያል (ቍ.4)?
2. መፍትሔ ሲገኝ የሙሴ ፈንታ ምን ነበረ?
3. እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ አንድ ዓይነት ፈተና ለምን ይደግማል? በእንተ ላይ ከደረሱ ፈተናዎች በትምህርታቸው ልብ ያደረግሃቸው አሉን?
4. ከአማሌቅ ጋር በነበረው ውጊያ፥ ሀ) የኢያሱና የወታደሮቹ፥ ለ) የሙሴ፥ ሐ) የአሮንና የሑር ፈንታ ምን ነበረ (8-13)?
5. በዚህ ውጊያ ከነበሩት ሰዎች ውስጥ ከየትኛው ጋር ራስህን አንድ ለማድረግ ይቀልሃል? ለምን?
6. ከዚህ ድል ኢያሱና ሕዝቡ ምን መማር ይገባቸው ነበር (14-16)?

ቍ,7 ማሳህ፤ በዕብራይስጥ መፈታተን፤ መራባ ማጉረምረም ማለት ነው። ይህን የመሰለ ታሪክ በተፈጸመበት ሌላ ስፍራ ደግሞ መሪባ ተባለ (ዘኁ.20፥2-13)።

ቍ,8 አማሌቅ፤ ከዔሳው ዝርያ የተገኘ ዘላን ሕዝብ (ዘፍ.36፥12)።

ቍ,9 ኢያሱ፤ የሙሴ አገልጋይ (24፥13)፤ ዕድሜው በዚህ ጊዜ 30 ዓመት ገደማ ነበረ።

ቍ.11 እጁን ባነሣ ጊዜ (እጆቹን ወደ ሰማይ በዘረጋ ጊዜ)፤ የዚህ ምልክት ትርጉም ለእኛ ፍጹም ግልጥ ባይሆንም እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲረዳ ልመናን፥ በጠላቶቹ ላይ ርግማንና ለወታደሮቹ ትእዛዝን የሚያጠቃልል ይመስላል (14-16፤ 1ሳሙ.15፥2-3፤ መዝ. 62(63)፥ 4)።

ቍ.14 ለመታሰቢያ በመጽሐፍ ጻፈው፤ ሙሴ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲጽፍ ሲታዘዝ እዚህ ይታያል።

ቍ.15 ያህዌህ ንሲ (እግዚአብሔር የድል ሰንደቅ ዓላማዬ ነው)።

<u>ሳምንት 21 ማክሰኞ</u> አሪት ዘጸአት 18

1. አማትን ስለ ማክበር ከሙሴ አርአያነት ምን ትማራለህ (ቍ.1-12፡24)?
2. ስለ ራስህ ሕይወት ታሪክ ስትገልጽ ችግርህን፥ድካምህን፥ ፈተናህን፥ ውድቀትህን፥ ድልህን፥...ወዘተ. በትክክልና በእውነት ትገልጣለህን (8)?
3. ዮቶር (የትሮ) ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ምን ተረዳ (9-12)?
4. ዮቶር ለሙሴ ምን ምክር ሰጠ (13-27)? ለምን?
5. ምክርን መቀበልና ኀላፊነትን ለሌሎች ማከፋፈል ታውቃለህን?

ቍ,1 የሙሴ አማት ዮቶር (የትሮ)፤ 3፥1 እና 2፥ 16-22 ተመ.።

ቍ,15 እግዚአብሔርን ለመጠየቅ፤ በእስራኤል የሕግ ሥራ ሁሉ እንደ መንፈሳዊ አገልግሎት ይቈጠር ነበር (21)።

ቍ.24 ሙሴ የአማቱን ቃል ሰማ፤ ዘሌ.19፥32።

ትንቢተ ሆሴዕ

እንደ አሞጽ ሆሴዕ ስለ ሰሜን መንግሥት፥ስለ እስራኤል ትንቢት ተናገረ፤ አገልግሎቱ ከአሞጽ አገልግሎት በመን ጀምሮ እስከ ሰማርያ መማረክ

ዘመን ድረስ ቢያንስ ለ32 ዓመታት ቀጠለ (1፥1)። በዚህ ወቅት ስለ እስራኤል አገር ሁኔታ በ9ኛው ሳምንት ስለ አሞጽ የተጻፈውን ተመልከት።

የሆሴዕን መልእክት ለመረዳት በእስራኤል የነበረውን ባዕድ አምልኮ ሁኔታ ልብ ማድረግ ያስፈልጋል። እስራኤላውያን ከከነዓናውያን አምልኮት ልዩ ልዩ ባህል፥ በተለይ የጉብረ ሥጋ ግንኙነትን ከያህዌ አምልኮት ጋር አደባልቀው ነበርና፥ ሆሴዕ «ግልሙትና» (የዝሙት ሥራ) ሲል መንፈሳዊ ከሀዲነትን ብቻ ሳይሆን ሴሰኝነታቸውን ያመለክታል። ሆሴዕ እንደ አሞጽ ይህ በደል ፍርድን በቅርብ ጊዜ እንደሚያመጣ ያስጠነቅቃል።

ስለ እስራኤል የእግዚአብሔርን ስሜት ለመግለጥ ሆሴዕ የሚስቱን ጋለሞታነትና ለሚስቱ የነበረውን የፍቅር ታሪክ ይጽፋል። በዚህ ዓይነት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት እጅግ ልባዊና የግልም መሆኑ ይታያል።

በምዕራፍ 1 እና 2 ላይ የጥቅሶች ቍጥርና ብዛት የተለያየ ስለሆነ በቅንፍ ውስጥ ያሉት ቍጥሮች አዲስ ትርጕምን ያመለክታሉ።

<u>ሳምንት 21 ረቡዕ</u> ሆሴዕ 1፥1-9፤2፥1-3(1፥10፡11፤2፥1)3፥1-5

1. የነቢርን ታሪክ በቅደም ተከተል ጻፍ (1፥2፡3፡6፡8፤ 3፥1-3)።
2. ሆሴዕና ነቢር እንደነና እንደባልና ሚስት ለመኖር ምን ያስፈልጋቸው ነበር (3፥3)?
3. የልጆቻቸው ስሞች ምን ያመለክታሉ (1፥4-9)?
4. የነቢርን መልሶ ከእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ጋር አነጻጽር (2፥1-3(1፥10፡11፤2፥1)፤ 3፥1፡4፡5)።
5. ይህ ታሪክ፥ ሀ) ለሕዝቡ፥ ለ) ለእንተ የእግዚአብሔርን ፍቅር ታላቅነት እንዴት እንደሚገልጥ አስላስል።

1፥2 ጋለሞታን ሴት (ዘማዊት ሴት)፤ እንዳንዶች ጎሜር ካጣች በኋላ እንዳመነዘረችና በዚያን ጊዜ ሆሴዕ ጠባይዋን እንደተረዳ ያስባሉ፥ ይህም ከእስራኤል ታሪክ ጋር ስለሚስማማ ነው።

1፥4 ኢይዝራኤል፤ እግዚአብሔር ይዘራል ማለት ነው። ኢዩ (ዮሁ) ትክክለኛውን ነገር ሲያደርግ መንፈሱ ልክ አልነበረም (2ነገ.10፥11፡30፡31)። እግዚአብሔር በንጉሥ ቤት ፍርድን «ይዘራል»፥ ደግሞም ወደፊት ለሚሆነው ለእስራኤል በረከት ይዘራል (2፥21-23)።

1፥6 ሉሩሃማ፤ አለምሕረት ማለት ነው፤ በእናቱ (በእስራኤል) አመንዝራነት ምክንያት ነው።

1፥9 ሉዓሚ፤ ሕዝቤ ያልሆነ ማለት ነው፤ ለጊዜው ከእግዚአብሔር የሕዝቡን መራት ያመለክታል (ሮም 11፥1-5)።

2፥1፡2(1፥10፡11)፤ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርገው ሆሴዕ ስለ ፍርድ ሲናገር አንድ አጭር አንቀጽ ስለሚመጣው በረከት ያስገባል። ሮም 11፥1-5።

ዓሚ፤ በዕብራይስጥ ሕዝቤ፥ ሩሃሚ ምሕረት ማለት ነው።

3፥1 የዘቢብ ጥፍጥፍን ቢመድጉ (የዘቢብ መሥዋዕት ለሚያቀኝ ለማትረብ ቢፈልጉም)።

3፥4፡5 የእስራኤል ምርኮን የመመለስ ዜመናት ያመለክታል።

<u>ሳምንት 21 ሐሙስ</u> ሆሴዕ 2፥4-25(2፥2-23)

1. ሆሴዕ የእስራኤልን አመንዝራነት በምን አኳኋን ገለጠ (ቍ.7(5)፤ 10(8)፤ 15(13)?
2. አንተ ከእግዚአብሔር መንገድ ብትወጣ መተላለፍህ እንደ እስራኤል ዓይነት ኃጢአት ይሆናልን? ያዕቆብ 4፥4 ተመ.።
3. እግዚአብሔር እውነተኛ በረከት ሁሉ ከእርሱ እንደሚመጣ እንዴት ያሳያል (11-14(9-12))?
4. እግዚአብሔር እስራኤልን እንደገና ወደ ራሱ እንዴት ይስባል (16-19(14-17))?
5. የእስራኤል መጨረሻ ሰላም(20(18))፥ ጎብረት ከእግዚአብሔር ጋርና(17፡18(19፥20)) በረከት 23-25(21-23) እንዴት ሊሆን ይችላል?
6. ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ውል ከቍ.16-25(14-23) ጋር አነጻጽር።

ቍ.7(5) ውሽሞቹ፤ እስራኤል ያመለከቻቸው (በአሊም (በአል የተባሉት ጣዖታት 15(13))፤ ምንብ፥ ልብስ፥ ወይንና ዘይት ከእነርሱ እንደተገኙ ሕዝቡ አመነ።

ቍ.17(15) የአኮርን ሸለቆ (የመከራንም ሸለቆ)፤ ኢያሱ 7፥24-26 ተመ.። አሁን ይህ «ሸለቆ» የተሰፋ በር ሆነ።

ቍ.18(16) በአሌ (በአል)፤ በአል የጣዖት ስም ሲሆን ትርጉሙ ጌታ ማለት ነው።

<u>ሳምንት 21 ዓርብ</u> <u>ሆሴዕ 4</u>

1. የእስራኤልን ኃጢአት ዘርዝር (ቍ.1-14)።
2. ይህን ሁሉ ኃጢአት እንዲሠሩ የልባቸው ሁኔታ እንዴት ነበረ?

3. የሕዝቡ ኃጢአት ከካህናት አካሔድ ጋር እንዴት የተያያዘ ነበር?

4. ‹‹እውቀት›› ምንድን ነው (6)? እውቀትን እንዴት ትረዳኃለህ?

5. በቍ.15-19 ለይሁዳ ምን ማስጠንቀቂያ ተሰጠ? ይህስ ለእንተ ምን ማስጠንቀቂያ ይሆናል?

ቍ.15 ጌልገል፤ የአሞጽ 4፥4ን ማስታወሻ ተመ.። በኋላ የባዕድ አምልኮ ስፍራ ሆኖ ነበር (9፥15)።

ቤትአዌን፤ የክፋት ቤት ማለት ሲሆን ለቤቴል (የእግዚአብሔር ቤት) የተሰጠ የአጬሞር ስም (5፥8፤ 10፥5፡8)።

ቍ.17 ኤፍሬም፤ ከአሥሩ ነገዶች አንደኛው፥ በመሆኑ እዚህ ላይ እስራኤልን ሁሉ ያመለክታል።

ሳምንት 21 ቅዳሜ — ሆሴዕ 5፥1-15፤6፥1-11

1. እስራኤል ወደ አምላኩ እንዳይመለስ ምን ከለከለው (5፥1-7)?

2. ብሔ፥ንቅዝና አንበሳ (5፥12፡14) በእስራኤልና በይሁዳ ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዴት ይመስላሉ (5፥8-14)?

3. የእስራኤል መንፈሳዊ ሁኔታ በግለጻ ደመና (ጉም)ና በጠል (ጤዛ) ለምን ተመሰለ (6፥1-10)?

4. እግዚአብሔር የማይተበለው መሥዋዕት እንዴት ያለ ነው (6፥6)?

5. በፍርድ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዓላማ ምንድን ነው (5፥15፤6፥11)?

6. ሃይማኖትህ እንደ እስራኤል ከአንገት በላይ ብቻ እንዳይሆን ምን ታደርጋለህ?

5፥1 ወሮቷ...በታቦር፤ በዚህ ቦታዎች ላይ አምልኮ የነበረ ይመስላል።

5፥7 ዳታሉቻን፤ ታሉ መንፈሳዊ ሁኔታቸውን ያመለክታል።

6፥6 ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን...፤ ይህ በመሥዋዕት ዋናው ነገር የለብን ሁኔታ ለመገለጥ እንጂ እግዚአብሔር ሥርዓቱን እንደሚንቅና አያስተምርም።

6፥7 እንደ አዳም ታሉ ኪዳንን ተላልፈዋል፤ አንዳንዶች በእግዚአብሔርና በአዳም መካከል የነበረው ግንኙነት ታሉ ኪዳን ባይባልም፥ ምሥጢራት (ምልክቶች)ና ተስፋ ማስጠንቀቂያም ነበሩበትና የታሉ ኪዳንን መልክ ይዞ ነበር ይላሉ፤ ሌሎች አዳም በተባለው ቦታ የሠሙን (ምናልባት አያሱ 3፥16 እና 7፥11ን ማያያዝ ይቻላል) ወይም ጠቅላላውን የአዳምን ዝርያ እንደሚያመለክት ያትታሉ፤ ያም ሆነ ይህ ትእዛዙን ጥሰው በመተላለፋቸው ሆሴዕ ወቅሳቸው።

ሳምንት 22 እሑድ — መዝሙር 21(22)

መዝሙር፤ ማንኛውም ክርስቲያን ይህን መዝሙር ሲያነብ ከመስቀሉ ሬት ይቆማል። ሆኖም በብሉይ ኪዳን ዘመን በመስቀል ላይ መሞት ያልታወቀ ዓይነት ትጣት ነበረ። ነገር ግን ዳዊት ይህን የተናገረው፥ ‹‹ከቢይ ስለ ነበረ›› የመሲሕን ሕማም፥ ሞትና ትንሣኤ አስቀድሞ በማየቱ ነው (ሐ.ሥ.2፥30-31)። ይህም በመሆኑ ከሌሎች መዝሙሮች ልቆ በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰ መሆኑን እንገነዘባለን።

1. የመዝሙረኛው ዋና ሥቃይ ምን ነበረ (ቊ.1፡2)?
2. ክስ ሲደርስበት እምነቱን ለማጽናት እንዴት ቻለ (3-10)?
3. ቊ.1 እና 11-18ን ከግቱ.27፡35-46 ጋር አነጻጽረህ የትንቢቱን ፍጻሜ ጠርዝር።
4. በቊ.19-21 እና በ22-24 መካከል ምን ልዩነት አለ? ምንስ ሆኖ ነበር?
5. ከሥቃዩ የሚገኘውን በረከት ጠርዝር (25-31)።
6. ከመርስቶስ ሕማም ምን በረከት ተቀበለ?A?

ቊ.14 ሰም፤ የድካም ምልክት

ቊ.22 ዕብ.2፡11-13 ተመ.።

ሳምንት 22 ሰኞ ሆሴዕ 7፡1-16፤8፡1-14

1. እስራኤል በምድኟ (7፡4-7)፡ ባልተገላበጠ ቂጣ (7፡8)፡ በርግብ (7፡11)፡ በቀስት (7፡16)ና በምድረ በዳ አህያ (8፡9) ለምን ተመሰለ?
2. እስራኤል ይትርታን ለመተበል ወደ እግዚአብሔር ለምን አልተመለሰም ነበር (7፡1-10፤ 8፡3፡12፡14)?
3. የእስራኤል ተስፋ በምን ላይ ነበረ (7፡11፤ 8፡2፡9፡11፡13፡14)?
4. እግዚአብሔር እስራኤልን በምን አካኋን ይመለከት ነበር (7፡2፡13፤ 8፡5፡13)?
5. እንደ እስራኤል ዕውር እንዳትሆን ምን ታደርጋለህ?

8፡9 እንደ ምድረ በዳ አህያ፤ ለማለመድ ፈጽሞ የማይቻል እንስሳ ነው።

ሳምንት 22 ማክሰኞ ሆሴዕ 9

መግቢያ፤ ሕዝቡ ከኃጢአታቸው ባለመመለሳቸው ምርኮን (9፡1-7)፡ የሕዝብ ብዛት መቀነስን(9፡8-17)፡የመሚያዎች መፍረስን፡ የቤተ መንግሥት መሻርንና የሕዝብ ወደ ባርነት መግባትን(10፡1-15) ያሰከትል ነበር።

1. እግዚአብሔር እስራኤልን በምን አካኋን ሊቀጣ ነበር?
2. እግዚአብሔር ይህን ሁሉ መዓት በሚወደው ሕዝብ ላይ ለምን አመጣ?
3. የእግዚአብሔር ፍቅርና ጽድቅ በእስራኤል ታሪክ ላይ እንዴት ይገናኛሉ (9፡10፡17)?
4. ይህ ምዕራፍ ስለ ኃጢአት ጠንቅ ምን ያስተምርሃል?

ቊ.9 ጊብዓ (ገባዖን)፤ ከፉ ወንጀል የተፈጸመበት ከተማ (መሳ.19)።

ቊ.10 ብዓልፌጎር (በዓልፐዖር)፤ እስራኤላውያን በባዕድ አምልኮና በዝሙት የተከፋ የተለዩበት ቦታ (ዘኍ.25)።

ሳምንት 22 ረቡዕ ሆሴዕ 10

1. እስራኤላውያን፥ ሀ) ሀብት ሲኖራቸው (ቊ.1)፥ ለ) ንጉሥ ሲጠፋባቸው (3፡7)፥ ሐ) መሠዊያዎች ሲፈርሱባቸው (2፡6፡8)፥ መ) ጦር ሠራዊቱ ሲሸነፍ (13-15) ምን አደረጉ?
2. ከፍርድ እንዲድኑ ምን ምክር ተሰጣቸው (11፡12)?
3. ብዙ ሀብትና የጦር ኃይል ለእግዚአብሔር ሕዝብ ለምን አደገኛ ነገሮች ይሆናሉ?
4. ለሕይወትህ ዋስትና እንዲኖርህ ምን ያህል ትደክማለህ?
5. ሀብትን ለመጠበቅ የሚበቃ ሰው ሆነህ በእግዚአብሔር ዘንድ የምትቈጠር መሆንህን ትገምታለህን?

ቊ.5 ስለ ቤትአዌን እምቦሳ (በቤትአዌን ስላለው የጥጃ ጣኦት)፤ 4፥15 እና ግስታወሻ፤ 1ነገ.12፥28፡29 ተመ.።

ቊ.11 የእስራኤል ሁኔታ ግበራየት እንደሚወድ ወይፈን (ዘዳ.25፥4) ወደ ቀንበር ሥራ ግለት፥ ከነፍነት ወደ ባርነት እንደሚጓዝ ነው።

ቊ.14 ሰልማን...፤ ምናልባት የአሦር ንጉሥ ሰልምናሶርን ያመለክታል (2ነገ.17፥3)፤ በጦርነት ጊዜ ብዙ ግፍና ጭካኔ በሴቶችና በልጆች ላይ ይፈጸም ነበር።

ሳምንት 22 ሐሙስ ሆሴዕ 11፥1-11(11፥1-12)፤ 12፥1-15(12፥1-14)

1. በመጀመሪያ እግዚአብሔር እስራኤልን በምን አኳኋን ወደደ (11፥1-4፤ ዘዳ.7፥6-8)?
2. እስራኤል እልከኛ ስትሆን እግዚአብሔር እንዴት ተመለከታት (11፥8-11)?
3. የእስራኤልን ሕዝብ አካሔድ ከያዕቆብ አካሔድ ጋር አነጻጽር (12፥1-6፤ (11፥12፤ 12፥1-5))።
4. እግዚአብሔር ከሕዝቡ ምንን ጠየቀ (12፥6-7 (12፥5-6))?
5. እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃጢአት ለምን ተበቀለ (12፥8-15 (12፥7-14))?
6. የእግዚአብሔርን ፍቅርና ቊጣ ስታስተውል በሕይወትህ ምን ለውጥ ታገኛለህ?

11፥8 አዳማ...ሲባዮ (ዶባይ)፤ እንደ ሶዶምና ገሞራ የጠፉ ከተማዎች (ዘዳ.29፥23)።

12፥3፡4 (12፥2፡3)፤ ዘፍ.25፥26፤ 28፥10-22 ተመ.።

ሳምንት 22 ዓርብ ሆሴዕ 13

1. የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ በምን አራት መንገዶች ተገለጠ (ቊ.3፡7-8፡15፡16)?
2. ለዚህ ፍርድ ምን አራት ምክንያቶች ተሰጡ (1-2፡4-6፡9፡16)?

3. ይሆን ሁሉ ስትመረምር ስለ ኃጢአት መሠረታዊ ሁኔታ ምን ትማራለህ?
4. እግዚአብሔር ሌላ ዕድል ለምን አልሰጣቸውም (14)? ለእግዚአብሔር ርኅራኄ ምን ውሳኔ አለ?
5. ለወደፊትስ ምን ተስፋ አለ (14፤ 1ቆሮ.15፥55)?

ሳምንት 22 ቅዳሜ — ሆሴዕ 14

1. እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ ኃጢአቱን በምን ዐይነት ሁኔታ መግለጥ ነበረበት (ቍ.1-3)?
2. አንተ ንስሓ ስትገባ ኃጢአትህን ዘርዝረህ መግለጥ ለምን ያስፈልግሃል?
3. እግዚአብሔር በመጨረሻ ሕዝቡን እንደሚባርክ ምን ዋስትና ሰጠ (4፡5፡8)?
4. በቍ.5-7 የተጻፉት ምሳሌዎች ስለ እስራኤል በረከት ሁኔታ ምን ያሳስባሉ?
5. ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዳወቁ ንስሓ ለመግባት ለምን ያመነታሉ? አንተስ አመንትተህ ታውቃለህ? ለምን?
6.* በዚህ ምዕራፍ የተገለጠውን የእግዚአብሔር ፍቅር ለጎሜር ከነበረው ከሆሴዕ ፍቅር ጋር አነጻጽር (ም.1-3)። ይሆንም ስታደርግ ለልጆቻቸው የተሰጡ ስሞችና አዲስ ስሞች ጠቅላላ የመጽሐፉን ሐሳብ እንዴት እንደሚያብራሩ ግለጥ።

ቍ.9 1ቆሮ.2፥14 ተመ.።

ሳምንት 23 እሑድ — መዝሙር 22(23)

መግቢያ፤ በዚህ መዝሙር በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት በሁለት ጉልህ የሆኑ ሥዕሎች ይታያል፤ አንደኛው ሥዕል ስለ እረኛውና ስለ በጉ (ቍ.1-4) ሲያሳየን፥ ሁለተኛው ደግሞ ስለ አስተናጋጁና ስለ እንግዳው (ቍ.5-6) ያመለክታል።

1. መዝሙሩ ስለ እግዚአብሔር እረኝነትና አስተናጋጅነት ምን ይገልጣል?
2. በእረኛው ጎላፊነት ለበጉ የሚያስፈልጉት ነገሮች ምንድን ናቸው ?
3. በእረኛውና በበጉ መካከል ያለው የቅርብ ግንኙነት በምን ዓይነት ቃላት ገለጠ?
4.* ሀ) እንቅስቃሴ ከዕረፍት ጋር፥ ለ) ፍርሃት ከመጽናኛ ጋር፥ ሐ) አደጋ ከዋስትና ጋር፥ መ) ፍላጎት ከአቅርቦት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ስታነጻጽር ልዩነቶቹ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሰው ምን ያሳያሉ?
5. «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው» ስትል ምን ማለትህ ነው?

ሳምንት 23 ሰኞ

ኦሪት ዘጸአት 19

መግቢያ፤ የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ከወጣ በኋላ በሦስተኛው ወር ወደ ሲና ተራራ ደረሰ፤ በዚያም ለአንድ ዓመት ሲቆይ ቃል ኪዳንና ሕግ፥ ሥርዓትም ተሰጡት።

1. እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ወደፊት ስለሚኖረው ግንኙነት ምን ዓይነት ሐሳብ አቀረበ (ቍ. 3-6)?
2. ሕዝቡ በምን አኳኋን መልስ ሰጠ (7፡8)?
3. እግዚአብሔር ለሕዝቡ በምን አዲስ መንገድ ራሱን ገለጠ (9፡11፡19)?
4. ይህ ምዕራፍ የእግዚአብሔርን ቅድስና እንዴት ይገልጣል (10-15፡20-25)?
5. በዚህ ዕለት ሕዝቡና ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ሲገናኙ ምን ሆኑ (16-20)?
6. የእስራኤልን ሕዝብ ጥሪ ከራስህ ጥሪ ጋር አነጻጽር።

ቍ. 4 በንስርም ክንፍ፤ ዘዳ. 32፡11 ተመ.።

ቍ. 6 የካህናት መንግሥት (እንደ ካህናትም ሆናችሁ ታገለግሉኛላችሁ)፤ የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ እንደ ካህናት ሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኙ፤ ደግሞም ለሌሎች ሕዝቦች እግዚአብሔርን ወከሉ፤ ዛሬ ይህ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ ይፈጸማል (1ጴጥ. 2፡5፡9)።

ቍ. 22 ካህናት፤ ከሲና በፊት ካህናት እንደነበሩ አልተጻፈም ስለዚህ ቃሉ ሽማግሌዎችን ሊያመለክት ይችላል (18፡12)።

ሳምንት 23 ማክሰኞ

ኦሪት ዘጸአት 20

1. እግዚአብሔር አሥርቱን ትእዛዛት ከመስጠቱ በፊት በምን ሁለት ነገሮች ላይ አተኩረ (ቍ. 1-2)?
2. የመጀመሪያዎቹ አምስቱ ትእዛዛት ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን ይገልጣሉ (3-12)?
3. ሰው ባለው ሁኔታና ሀብት እንዲደሰት በመጨረሻዎቹ ስድስት ትእዛዛት እንዴት ተገለጠ (12-17)?
4. እስራኤል ትእዛዛቱን እንዲጠብቅ እግዚአብሔር ምን አደረገ (18-26)?
5. በአሥርቱ ትእዛዛት መሠረት ራስህን መርምረህ ኃጢአትህን አንድ በአንድ ተናዘዝ።
6. * ለወደፊቱ በየጊዜው ራስህን እንድትመረምር እያንዳንዱን ትእዛዝ የተላለፍህበትን መንገድ ዘርዝር።

ቍ. 4 የማናቸውንም...ምስል ለአንተ አታድርግ፤ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኘው በቃሉ እንጂ በማናቸውም በሚታይ ነገር አልነበረም(ዘዳ. 4፡12)፤ ምስሎች እግዚአብሔር በአንድ ስፍራ እንደሚወሰንና ባሕርዩ በግዙፋዊ ዓይነት እንዲተረጐም ተጽዕኖ ያደርጋሉና።

ቍ. 11 ሰንበት ስለ ማክበር፤ በዘዳ. 5፡15 ተጨማሪ ምክንያት ይሰጣል።

ሳምንት 23 ረቡዕ — ኦሪት ዘጸአት 21

መግቢያ፤ ከአሥርቱ ትእዛዛት ቀጥሎ እነዚህን ትእዛዛት ለመፈጸም ለሕዝብ ሥርዓት (ሕግ) ተሰጠ።

1. በቁ.1-11 የሚገኙት ትእዛዛት በባርነት ቀንበር ሥር እንኳን የሰውን ክብር ምን ያህል ይጠብቃሉ?
2. የዚህን ዓይነት ባርነት እስራኤል በግብጽ ከነበረበት ባርነት ጋር አነጻጽር (20፥2)።
3. በቁ.12-35 የሚገኙትን ትእዛዛት ዘርዝር።
4. የሞት ፍርድ በሚያስከትሉት በደሎች ላይ አስምር፤ ይህ ፍርድ ለእነዚህ በደሎች ለምን ተወሰነ?
5. ለሌሎች በደሎች ምን ቅጣት ተወሰነ? በምንስ ምክንያት?
6. * በዛሬው ማኅበራዊ ኑሮ፥ ሀ) የተበዳይ፥ ለ) የበዳይ መብትና ክብር ምን ያህል ይጠበቃሉ?

ቁ.24 ዓይን ለዓይን፤ ሕጋዊ ውሳኔ የተሰጠው ቅጣቱ ከመጠን በላይ እንዳይሆንና እንደ በደሉ እንዲሆን የተጎዳው ሰውም በግል በቀልን እንዳይፈልግ ነበረ። ሰው በፍቅር ቢመላለስ ግን አስተያየቱ የተለየ ይሆናል (ማቴ. 5፥38-48)።

ሳምንት 23 ሐሙስ — ኦሪት ዘጸአት 22

1. አውቆ በሚሰርቅ በቸልተኝነት በሚያጠፋ ሰው ላይ በሚሰጥ ቅጣት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው (ቁ.1-15)? ከአንተ ቸልተኝነት የተነሣ በሌሎች ላይ ምን ጉዳት ሊደርስ ይችላል?
2. ሰው ጥፋተኛ አለመሆኑን ለማረጋገጥ እንዴት ይችል ነበር (8፥11)? በጌታ ፊት የምትናገረው ቃል ምን ዋጋ አለው?
3. መተኛውን መጪቆን እንደ ትልቅ ኃጢአት ለምን ይቆጠራል (21-24)?
4. ለድሆች የምታደርገው ችሮታ የአምላክህን ባሕርይ ይገልጣልን (25-27)?
5. እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ አስቀድሞ እንዲከበር ምን ትእዛዛትን ሰጠ (18-20፤28-31)?
6. እግዚአብሔር በሕይወትህ የመጀመሪያው እንዲሆን ምን ታደርጋለህ?

ቁ.1-4 ሌባ እንኳን ከሚገባው በላይ እርምጃ እንዳይወሰድበት ሕግ እንደከለከለ ግስተዋል ይገባናል።

ቁ.16-20 የግይገባ ግብረ ሥጋና ባዕድ አምልኮ በነዚህ ቍጥሮች አንድ ላይ ይገኛሉ፥ ምክንያቱም በአሕዛብ ዘንድ አገር እንዲለማ የሚቀርበው የመሥዋዕት ሥርዓት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ጋር ይፈጸም ነበር።

ሳምንት 23 ዓርብ — ኦሪት ዘጸአት 23

1. ፍርድ ሁሉ በትክክለኝነት እንዲፈጸም ምን ትእዛዝና ማስጠንቀቂያ ተሰጠ (ቁ.1-9)?

2. «ዕረፍት»ኑሮህ ሁሉ ትከከለኛ ስፍራ ይዞአልን (10-13)?
3. የምስቱ ዓመታዊ በዓላት ዓላማ ምንድን ነው (14-19)?
4. ከሥራህ ፍሬ ለእግዚአብሔር ምን ያህሉን ትሰጣለህ?
5. እስራኤል ለእግዚአብሔር ሲታዘዝ ምን ተስፋ ነበረው (20-33)?
6.* ተስፋህን ከእስራኤል ተስፋ ጋር አነጻጽር።

ቍ.19 ጠቦትን በእናቱ ወተት አትቀቅል፤ ዝናብ እንዲዘንብ በከነዓናውያን አምልኮት ይደረግ የነበረ ይመስላል፤ ይህንንም ማድረግ በእግዚአብሔር የተሰጠውን ሕይወት መንቀፍ ነበረ።

ሳምንት 23 ቅዳሜ

ኦሪት ዘጸአት 24

መግቢያ፤ በፊት ሕዝቡ ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ ቃል ተስጥቶአቸው ነበር(19፥8)። አሁንም የእግዚአብሔር ሕግ ከተነበበላቸው በኋላ ሕዝቡ በሙሴ አማካይነት ቃል ኪዳን ሲገቡ እናያለን።

1. ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ሲገቡ፥ ሀ)ሙሴ፥ ለ)ሕዝቡ፥ ሐ)አዛውንቶች ምን አደረጉ (ቍ.1-11)?
2. ደሙ፥ ሀ) በመሠዊያው፥ ለ) በሕዝቡ ላይ በመረጨቱ ምን ታስተውላለህ?
3. በአዲስ ኪዳን ውስጥ መገኘትህን በምን ታረጋግጣለህ (1ጴጥ.1፥1-2)?
4. ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ፥ ሀ) ለሕዝቡ፥ ለ) ለአዛውንቶች፥ ሐ) ለሙሴ ምን ዕድል ተሰጠ (1፡2፡9-18)?
5. የዚህ ዕድል ልዩነት ምክንያት ምን ይመስልሃል? ከእግዚአብሔር ጋር ያለህ ግንኙነት ቅርብ ነው ወይስ ሩቅ? ለምን (ዕብ.10፥19-22)?
6.* የአዲስ ኪዳንን፥ ሀ)መካከለኛ፥ ለ)አባሎች፥ ሐ)ሕግ፥ መ)መሥዋዕት፥ ሠ)ደም መርጨት፥ ረ)የማረጋገጫ ግብጥ ከብሉይ ኪዳን ጋር አነጻጽር (1ቆሮ.11፥23-26፤ ገላ.3፥19-20፤ ዕብ.7፥22፤ 8፥5-6፤ 9፥18-22፤ 1ጴጥ.1፥1-2)።

ቍ.4 የእግዚአብሔርን ቃሎች ጻፈ፤ ምናልባት ዘጸ.20፥22-23፥33፤ ይህም «የቃል ኪዳን መጽሐፍ» ይሆናል (7)።

ቍ.8 የቃል ኪዳኑ ደም፤ ቃል ኪዳኑን አተመ፤ አጸና፤ አረጋገጠም። ደሙ በመሠዊያው ላይ እግዚአብሔር ይቅር ብሎ እንደ ራሱ ሕዝብ እንደተቀበላቸው፥ በሕዝቡም ላይ የመታዘዝ መሐላ እንደነበረ ያሳያል (ዕብ.9፥18-19፤ 1ጴጥ.1፥1-2)።

ቍ.10 የእስራኤልን አምላክ አዩ፤ እግዚአብሔር በሙሉ ባሕርዩና ክብሩ ሳይሆን በከፊል የታያቸው ይመስላል (33፥20፡23)።

ቍ.11 በሉም ጠጡም፤ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሰላም ሲገኝ የደኅንነት መሥዋዕት ይበላ ነበር፤ የሚበላውም ለኃጢአት ማስተስሪያ የሚቃጠል መሥዋዕትን ካቀረቡ በኋላ ነበር (5)።

ቍ.13፡14 ኢያሱ...አሮን...ሖር፤ 17፥9፡10 ተመ.።

ሳምንት 24 እሑድ — መዝሙር 23(24)

መግቢያ፤ ይህ መዝሙር ዳዊት የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ኢየሩሳሌም ሲያመጣ የተዘመረ ይመስላል (2ሳሙ.6፥1-19)። የዘማሪዎቹ ሁለት ቡድኖች በቁ.3፥7-10 የሚገኙትን ጥያቄዎችና መልሶች እየዘመሩ በሰልፍ ወደ ጽዮን ተራራ ሲቀርቡ በወይነ-ጎሊናችን ማየት እንችላለን።

1. ዳዊት ሀ) ምድርን (ቁ.1-2) ለ) የጽዮን ተራራን ሲያይ ስለ እግዚአብሔር ምን ተገነዘበ?
2. በቁጥር 3 የሚገኘው ጥያቄ በዳዊት ሐሳብ ለምን ተነሣ (2ሳሙ. 6፥6-8)?
3. በቅድስናው ስፍራ ለመቆም ማን ብቃት አለው (4-6)?
4. ዘማሪዎቹ በቁጥር 7-10 የተመለከተውን ሲዘምሩ ሐሳባቸውን ዘርዝረህ አብራራ።
5. በእነዚህ ቁጥሮች የሚገኙትን ሐሳቦች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንዴት ታገናኛቸዋለህ?
6. ይህ መዝሙር ልብህን እንዴት ይነካል? ለምን?

ቁ.3 ወደ እግዚአብሔር ተራራ፤ ወደ ጽዮን ተራራ፤ የመዝ.2፥6ን ማስታወሻ ተመ.።

ቁ.7-10 ብዙዎች እነዚህ ቁጥሮች ክርስቶስ በዕርገቱ ወደ ሰማይ መግባቱን እንደሚያመለክቱ ይቈጥራሉ (ኢሳ.24፥23)።

ቁ.7 በሮች፤ ሰልፍ ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ጽዮን መድረሱን ያመለክታል።

ቁ.10 የጭፍሮች አምላክ፤ ቃሉ የእስራኤልን ጭፍሮች (1ሳሙ.17፥45)፥ እንዲሁም ደግሞ የሰማይን ሠራዊት (1ነገ. 22፥19) ያጠቃልላል።

ሳምንት 24 ሰኞ — ኦሪት ዘጸአት 25

መግቢያ፤ እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ፊት ፊት እየሄደ መርቶአቸው ነበር (14፥19)፥ አሁን ግን በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ ሲናገር በሕዝቡ መካከል ለመኖር እንደወሰነ ገለጠ (8)። ሰው ግን ወደ እግዚአብሔር በኃጢአት ምክንያት እንዲሁ መቅረብ አይችልምና፥ መሥዋዕት ማቅረብ ያስፈልገዋል። አቤል ከዔደን ገነት ውጭ መሥዋዕትን አቀረበ፤ ኖኅ ከመርከብ ሲወጣ መሥዋዕትን አቀረበ፤ አብርሃም በጉዞዎቹ ላይ መሠዊያዎችን እየሠራ መሥዋዕቶችን ያቀርብ ነበር፤ ሙሴ በሲና ተራራ ላይ መሠዊያን ሠርቶ መሥዋዕትን አቀረበ። አሁንም ሰዎች ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ስለ መሠዊያ አሠራርና ስለ መሥዋዕት ሥርዓት እግዚአብሔር ጥብቅ ትእዛዛትን ሰጠ። አዲስ ኪዳንን የሚያነቡ የመሥዋዕት ሥርዓት ሁሉ በክርስቶስ መፈጸሙን ያውቃሉ (ዕብ. ም.7-10)።

1. ሙሴ ስለ ቤተ መቅደስ አሠራር ምን ታዘዘ (ቁ.1-9)?
2. እግዚአብሔርን ለማገልገል ምን ችሎታና ተሰጥዎ አለህ?

3. የታቦቱን ቅርጽ በሥዕል ለማስቀመጥ ሞክር። በውስጡ ምን ተገኘ? በላዩ ላይስ ምን ነበረ (10-21)?

4. የስርየት መክደኛ ዓላማ ምን ይመስልሃል (22)?

5. የገበታው (የጠረጴዛው) ዓላማ ምንድን ነው (23-30)?

6. የመቅረዝ ዓላማስ ምንድን ነው (31-40)?

ቍ.3 ወርቅ፣ ብር፣ ናስም፣ ምናልባት በምድረ በዳ ላይ ይገኙ ነበር፣ ወይም ከግብጻውያን ተገኝተው ይሆናል (12፣35)።

ቍ.8 መቅደስ (ቤተ መቅደስ)፣ የተባረከ የተለየ ስፍራ።

ቍ,9 ማደሪያው (ድንኳን)፣ የመቅደሱ ዋና ክፍል።

ቍ.10 ታቦት፣ በመቅደሱ ውስጥ ዋናው የተቀደሰው አካል። ክንድ፣ አምሳ ሳንቲ ሜትር ያህል ነው።

ቍ,11 ወርቅ፣ እግዚአብሔር በሚያድርበት፣ በሚገለጽበት መቅደስ የሚገኙት ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ በወርቅ ተለበጡ።

<u>ቍ.16 ምስክር</u>፣ ትእዛዙቱ የተጻፉባቸው ሁለቱ ጽላት።

ቍ.17 የስርየት መክደኛ፣ ሰው ኃጢአተኛ ስለሆነ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ኃጢአቱ ከእግዚአብሔር ፊት እንዲከደን ያስፈልገዋልና፣ የእግዚአብሔር ሕግ ከተጻፈበት ጽላት በላይ የስርየት መክደኛ መገኘቱ የእግዚአብሔርን ምህረት ያብራራል።

<u>ቍ.18 ኪሩቤል</u>፣ ዘፍ.3፣24ና ማስታወሻ ተመ.።

ቍ.30 የገጽ ኅብስት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ሥርዓት ምክንያት ባይሰጥም፣ ኅብስቱ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት በመቅረቡና በመገኘቱ እግዚአብሔር የሰው መጋቢ መሆኑን ማስተዋል እንችላለን (ዘሌ.24፣5-9)።

ሳምንት 24 ማክሰኞ <u>አሪት ዘጸአት 26</u>

1. አሥሩ መጋረጃዎች ከምን ተሠሩ? በምን ተያያዙ (ቍ.1-6)?

2. መጋረጃዎቹ ከፀሐይና ከዝናብ እንዴት ይጠበቁ ነበር (7-14)?

3. የድንኳኑ ውበት በውስጥ ነው ወይስ በውጭ?

4. ድንኳኑ ለመንገድ ጉዞ ምቹ እንዲሆን እንዴት ተዘጋጀ (3-6፣15-30)?

5. ሁለቱ ልዩ መጋረጃዎች ከምን ተሠሩ የተሰቀሉት የት ነበረ (31-37)? ዓላማቸውስ ምን ነበረ?

6. በሕይወትህ ውስጥ ውበት የት ላይ ይታያል? ወደ እግዚአብሔር በምትቀርብበት ሁኔታ ወይስ በውጭ መልክህና አካሔድህ?

<u>ቍ.33 መጋረጃው</u>፣ ቅድስተ ቅዱሳን የተባለው የድንኳኑ ውስጠኛ ክፍል ይጨልም ነበር፣ ሊቀ ካህናት ብቻ በመጋረጃው ወደዚህ ክፍል ይገባ ነበር፣ ይህም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ (ዘሌ.16፣11-17፣ ዕብ.9፣6-7)። ከክርስቶስ ሥራ የተነሣ አማኙ በአዲስ ኪዳን ዘመን በአዲስ መንገድ ወደ እግዚአብሔር ይቀርባል (ማር.15፣38፣ ዕብ.10፣19-22)።

ሳምንት 24 ረቡዕ አሪት ዘጸአት 27

1. ከዚህ መሠዊያ አሠራር ስለ ዓላማው ምን ታስተውላለህ (ቍ.1-8)?

2. «ከተራራው እንዳሳየህ ምሳሌ...» የሚለው ትእዛዝ ስንት ጊዜ ተደገመ (25፥9፡40፤26፥30፤27፥8)? ለምን (ዕብ.8፥5)?

3. ለሙሴ የተሰጡትን ትእዛዛት እግዚአብሔር ከሚያዝዝህ ጋር አነጻጽረህ መታዘዝህን መርምር።

4. የድንኳኑን አደባባይ ክልል ጨርቅ ከድንኳኑ ጨርቅ ጋር አነጻጽር።

5.* ጠቅላላው የድንኳኑ አሠራርና አቀማመጥ የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንዴት ያብራራል? ሰውስ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብበትን መንገድ እንዴት ያሳያል?

ቍ.3 ናስ (ነሐስ)፤ ለእግዚአብሔር ቅርብ የነበረው ዕቃ በመርቅ፥ሩቅ የነበረው በርካሽ ናስ ይለበጥ ነበር።

ቍ.9 ጥሩ በፍታ (ቀጭን ሐር)፤ ለእግዚአብሔር ቅርብ የነበረው ጨርቅ በብዙ ዓይነት ቀለም፥ሩቅ የነበረው ደግሞ በነጭ ብቻ ይሠራ ነበር።

<u>ሳምንት 24 ሐሙስ</u> <u>አሪት ዘጸአት 28</u>

1. ሊቀ ካህናትና ካህናት እንዲሆኑ እነማን ተመረጡ (ቍ.1-5)?

2. ልዩ ልብስ ለምን አሰፈላጊ ሆነ (3-4)?

3. ስድስቱን ልዩ የክህነት ልብሶች ዘርዝር (4)። ለካህናት ደግሞ አስፈላጊ የነበረ ሰባተኛው የተራ ሰው ልብስ ምን ነበረ (42)?

4. ሰንጠረዥ አዘጋጅተህ ለእያንዳንዱ ልብስ፥ ሀ)ልዩ አሠራሩን፥ ለ)የተለበሰበትን የአካል ክፍል፥ ሐ)ዓላማውን ግለጥ (6-43)።

5. አንድ ሰው ዛሬ ለእግዚአብሔር ልዩ አገልግሎት እንዴት ሊሾም ይገባል (41)? በራሱ ነው ወይስ በሌላ?

6.* የእስራኤል ሊቀ ካህናት ልብሰ ተክህኖ ሲለብስ የክርስቶስን ሥራ እንዴት ያብራራል?

ሊቀካህናቱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ(39)፥ሰግያዊ (31)፥ውክልና ያለውና (12፡29)፥ ቅዱስ (36-38) መሆኑ በልብሱ ይታያል፤ አሮን የነገዶችን ስሞች በጫንቃዎቹ (የጦልበት ስፍራ)ና በልቡ ላይ (የፍቅር ስፍራ) በመሸከሙ ውክልናውን አሳየ።

ሳምንት 24 ዓርብ አሪት ዘጸአት 29፥1-37

መግቢያ፤ አሮንና ልጆቹ ልብሰ ተክህኖዎቻቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ግዕረግም ግግኘት ነበረባቸው።

1. ሙሴ ለአሮንና ለልጆቹ የክህነት ግዕረግ ሲሰጥ ምን ታዘዘ(ቍ.1-9)? ለእያንዳንዱ ሥነ ሥርዓት ምን ምክንያት ነበረ?

2. የሦስቱ እንስሳት መሥዋዕት ዓላማ ምን ነበረ (14፡18፡26)?

3. አሮንና ልጆቹ በሚሠዉአቸው እንስሳት ራስ ላይ እጆቻቸውን በመጫናቸው ምን ታስተውላለህ (10፡15፡19)?

4. በሁለተኛው አውራ በግ ደም የተቀደሱት ሦስቱ የካህናት አካል ክፍሎች ምን ነበሩ (20)? ቅደም ተከተላቸውን በመገንዘብህ ስለ ካህናት አገልግሎት ምን ታስተውላለህ?

5. አሮንና ልጆቹ አገልግሎታቸውን ሲጀምሩ ምን አደረጉ (24፥32-33)?

6. ከዚህ ሁሉ ሥርዓት ለራስህ ሕይወትና መንፈሳዊ አገልግሎት ምን አርአያ ታገኛለህ?

ቍ.7፥21 የቅብዓት ዘይት፤ ሰዎች ለተለየ አገልግሎት ኃይልን እንዲቀበሉ ይቀቡ ነበር (1ሳሙ.16፥13፤ 1ነገ.19፥16፤ ኢሳ.61፥1፤ ሉቃ.4፥17፤ ሐ.ሥ.1፥38፤ 2ቆሮ.1፥21)።

ቍ.10 እጆቻቸውን ...ይጭናሉ፤ ዘሌ.16፥21 ተመ.።

ቍ.24 ...28 ለሚወዘወዝ ቍርባን ,..የማንሣት ቍርባን፤ ካህናት መጀመሪያ መባውን በመወዝወዝ ከምስጋና ጋር ለእግዚአብሔር አቀረቡ፤ በኋላም ከመሥዋዕቱ አንዳንድ ክፍል ለእነርሱ ሆነ።

ቍ.36 መሠዊያውን ታነጻዋለህ፤ በሰው ስለ ተሠራ እንደ ርኩስ ሳይቆጠር አልቀረም።

<u>ሳምንት 24 ቅዳሜ</u> አሪት ዘጸአት 29፥38-46፤ 30፥1-38

1. የዕለት እሳት ቍርባን፥ ሀ) ሥርዓት፥ ለ)ጊዜ፥ ሐ)ዓላማው ምን ነበረ (29፥38-42)?

2. ጠቅላላው የመገናኛ ድንኳን ዓላማ ምን ነበረ (29፥43-46)?

3. እግዚአብሔር ከአንተ ጋር በምን ዓይነት መንገድ ይኖራል?

4. ለመቅደስ አገልግሎት ምን ዓይነት ሁለት ሌሎች ዕቃዎች ተሠሩ (30፥1-10፥17-21) ? ዓላማቸውስ ምን ነበረ?

5. በሕዝብ ቈጠራ ጊዜ ለእግዚአብሔር ምን ይሰጥ ነበር (30፥11-16)? ለምን?

6. የቅብዓት ዘይት (30፥22-33)፥ የቅዱስ ዕጣንም (30፥24-38) አገልግሎት ለምን ተደነገገ?

30፥12 የነፍሱ ቤዛ፤ 13፥13 ተመ.።

30፥13 ግማሽ ሰቅል (አንድ ጥሬ ብር)፤ በኋላ የቤተ መቅደስ ዓመታዊ ግብር ሆነ።

አልፎ የሚቈጠር ሁሉ (ከሕዝብ ቈጠራ ውስጥ የሚገባ እያንዳንዱ ሰው)

30፥29 ቅድስተ ቅዱሳን ይሆናሉ፤ ከካህናት ያልሆነ ሰው ቢነካው የሞት ፍርድ ነበረበት (2ሳሙ.6፥6-7)

<u>ሳምንት 25 እሑድ</u> <u>መዝሙር 24(25)</u>

1. ዳዊት የተጨነቀባቸውን ነገሮች ዘርዝር (ቍ.2፥7፥11 ፥16-19፥22)?

2. ልመናውን ሲያቀርብ ከእግዚአብሔር ባሕርያት የትኞቹን ጠቀሰ (1-7፥11፥16-22)?

3. ስለ እግዚአብሔር ሲያሰላስል እግዚአብሔርን የሚፈሩት ስለሚያገኙት በረከት ምን ተረዳ (8-10፥12-15)?

4. በዳዊት ጸሎት ጊዜ ልመናና ማሰላሰል አንድ ላይ በመገኘታቸው፥ ወደ እግዚአብሔር ስለመቅረብ ምን ትማራለህ?

5. በኃጢአት ምክንያት ችግር ቢገጥምህ፥ በዚህ መዝሙር የሚገኘው የዳዊት ምሳሌ እንዴት ሊረዳህ ይችላል?

6. ዳዊት ከችግሩ የተነሣ፥ ስለ ሀ)ራሱ ሕይወት (4)፥ ለ)እስራኤል (22) ምን ተማረ?

ቍ.13 ዙሩም ምድርን ይወርሳል፤ እግዚአብሔር በእስራኤል ለእያንዳንዱ ሰው ርስት ሰጥቶ ነበርና፥ ሰዎች ሲታዘዙለት ርስታቸውን ለተከታይ ትውልድ የማስተላለፍ ቋሚ ተስፋ ነበራቸው።

ሳምንት 25 ሰኞ አሪት ዘጸአት 31፥1-18፤32፥1-14

1. የእግዚአብሔር መንፈስና የሰው ሥነ ጥበብ በመገናኛው ድንኳን ሥራ እንዴት ተገናኙ (31፥1-11)?
2. ለሥነ ጥበብና ለሥነ ጥበብ ለሚተዳደሩ ሰዎች ያለህ አመለካከት ከዚህ አንቀጽ ጋር ይስማማልን?
3. ሰንበት ለእስራኤል ሕዝብ የምን ምልክት ሆነ (31፥12-18)?
4. ሙሴ በተራራው ላይ የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰማና ጽላቶቹን ሲቀበል ሳለ፥ ሕዝቡ ምን አደረጉ (32፥1-6)? ለምን? (32፥1ን ከ24፥7 ጋር አነጻጽር)።
5. አሮን ምን ለማድረግ ሞከረ (32፥5)? ውጤቱ ግን ምን ሆነ (32፥6)? የአሮንን ስሕተት ዘርዝር (32፥1-6ን ከ24፥ 14ጋር አነጻጽር)።
6. እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳያጠፋ ሙሴ የሰጠውን ምክንያት ዘርዝር፤ አንተ እንደዚህ ትጸልያለህን?

32፥5 ነገ የእግዚአብሔር በዓል ነው፤ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ፍጹም እንዳይረሱ አሮን የሞከረ ይመስላል።

32፥6 ሊዘፍኑም ተነሡ፤ ሌሎች ሕዝቦች በመሥዋዕት በዓል ጊዜ እንደሚያደርጉት ሁሉ፥ እስራኤልም በባዕድ አምልኮአቸው ጊዜ የጣዐረ ሥጋ ግንኙነት የፈጸሙ ይመስላል (1ቆሮ.10፥7)።

ሰምንት 25 ማክሰኞ አሪት ዘጸአት 32፥15-35፤33፥1-23

1. ሙሴ በሕዝቡ ላይ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ዘርዝር (32፥19-30)።
2. አሮን ሲወቀስ ምን መልስ ሰጠ(32፥21-24)? አንተስ ስትወቀስ እውነትን ሁሉ ትናገራለህ?
3. በሰው ላይ ከተቈጣህና እርምጃ ከወሰድህ በኋላ በማሥቱ ለዚያው ሰው እንደ ሙሴ መጸለይ ትችላለህን (32፥19-22፤31-32)?
4. በመጨረሻ ኃጢአታቸውን እንዲተዉ ሕዝቡን የገፋፋቸው ምን ነበረ (33፥1-6)?
5. ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ይገናኝ ነበር (33፥7-11)?
6. ሙሴ ምን ሦስት ነገሮችን ለመነ? ምን መልስ አገኘ (33፥12-23)?
7. የሕዝቡንና የሙሴን ምኞት ከራስህ ምኞት ጋር አነጻጽር።

32፥26 የሌዊም ልጆች ሁሉ፤ የሙሴና የአሮን ወገኖች።

33፥11 ፊት ለፊት፤ ዘኍ.12፥6-8 ተመ.።

33፥19 የምምረውንም እምራለሁ፤ እግዚአብሔር ከሁሉ በላይ ሆኖ በግዳን ሥራ ፈቃዱን እንደሚፈጽም ያረጋግጣል (ሮም 9፥15)።

ሳምንት 25 ረቡዕ — ኦሪት ዘጸአት 34

1. ሙሴ እንደገና ወደ ተራራው ሲመለስ እግዚአብሔር ራሱን በምን አኳኋን ገለጠለት (ቊ.5-7ን ከ33፥19 ጋር አስተያይ)?
2. እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተስፋ ሲሰጥ በየትኞቹ ትእዛዛት ላይ አተኩረ (10-26)?
3. ከእነዚህ ትእዛዛት በተለይ የአሁኑን ሕይወትህን አሁን በሚመለከቱት ላይ አስምር።
4. ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘቱ ምን ሆነ? ሕዝቡም ይህን ሲያዩ ምን ተሰማቸው (29-35)?
5. ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘትህ ምን ለውጥ በሕይወትህ ተገኘ? ይህ ለውጥ እንዴት ይታደላል? ሰዎችስ ስለሕይወትህ ለውጥ ምን ይላሉ?

ቊ.1 እጽፍባቸዋለሁ፤ ሙሴ ቃላቱን በእጁ ቢጽፍም እንኳን ደራሲው እግዚአብሔር ነው (27)።

ቊ.13 የማምለኪያ ዐፀዶቻቸው (አሼራ የተባሉች አምላካቸው ምስሎች)።

ቊ.14 ቅንእት ያለው አምላክ (ቀናተኛ)፤ እግዚአብሔር ለእርሱ የሚገባው ክብርና ፍቅር ለሌላ እንዳይሰጥ መፈለጉን ያሳያል (20፥4-6)።

ቊ.21 ሥራ በሚበዛበት ጊዜ እንኳን የእረፍት ሕግ መከበር አለበት።

ቊ.26 የ23፥19ን ማስታወሻ ተመ.።

ቊ.33 በፊቱ መሸፈኛ አደረገ፤ ሕዝቡ ሙሴን እንዲያከብሩ የከብሩ መቀነስ እንዳይታይ አስፈላጊ ነበር (2ቆሮ.3፥7-18)።

ሳምንት 25 ሐሙስ — ኦሪት ዘጸአት 35

መግቢያ፤ ም.35-39 የም.25-31ን ሐሳብ ስለሚደግሙ ዛሬና ነገ በምናደርገው ጥናት በአዳዲስና ተጨማሪ ነገሮች ላይ ብቻ እናተኩራለን።

1. ሙሴ ስለመገናኛው ድንኳን ሥራ ትእዛዝ ከማስተላለፉ በፊት ምን አዘዘ (ቊ.1-3)? ለምን?
2. ሰዎች ለመገናኛው ድንኳን መባን ለመስጠትና ሥራውን ለመሥራት ምን ያነሣሣቸው ነበር (4-29)?
3. እጉት መባን ለመስጠት ወይም ሥራን ለመሥራት ምን ይገፋፋሃል? መልስህ ሕግን መታዘዝ፥ ከሌሎች ጋር መወዳደር፥ ይሉኝታ፥ የመሪ ተጽዕኖ፥ ለተቸገሩት ርኅራኄ፥ ለክርስቶስ ፍቅር፥ ለወንጌል መስፋፋት የጋለ መንፈስ ወይስ የመንፈስ ቅዱስ ሸክም ይሆናል? መልስህን ከ2ቆሮንቶስ 9፥7 ጋር አስተያይ።
4. ቊ.30-35 በ31፥1-11 ሐሳብ ላይ ምን ይጨምራል (በተለይ ቊ.35፥34 ተመ.)?
5. ይህስ በሥራህ ምን ስፍራ አለው? ለምን?

ቍ.2 ሰንበት የተቀደሰ ቀን፤ ሕዝቡ የመገናኛውን ድንኳን እንኳን ሲሠሩ ሰንበትን እንዲያከብሩ ታዘዙ። በልዩ ልዩ ምክንያትና ብዙ ጊዜ ሰንበትን ስለማክበር ተነገረ (20፥8-11፤ 23፥12፤ 31፥12-17፤ 34፥21፤ 35፥1-3፤ ዘዳ.5፥12-15)።

ቍ,10 ጥበበኞች ሁሉ፤ ሁለቱ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ችሎታ ያላቸው ሁሉ ደግሞ በእግዚአብሔር ሥራ ድርሻ አላቸው (31፥1-6)።

ቍ.20-29 የ25፥1-9 ትእዛዝ ሲፈጸም የሴቶችና የመሪዎች ድርሻ ተለይቶ ይታያል።

ሳምንት 25 ዓርብ

ኦሪት ዘጸአት 36፥1-40፥16

መግቢያ፤ በም. 25-27 ስለሚገኙት ትእዛዛት መፈጸም በዛሬው ምንባብ እናገኛለን፤ በም.25-27 ትእዛዙ መጀመሪያ ስለ ታቦቱና ስለ ሌሎች ዕቃዎች ተሰጥቶ ነበር፤ አሁን ግን መጀመሪያ ድንኳኑ ሲተከል እያናለን።

1. ም.36-39 ስታነብ :-

ሀ) የሥራውን ቅደም ተከተል ዘርዝር።

ለ) «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው» የሚሉትና የመሳሰሉት ሐረጎች የሚገኙባቸውን ቍጥሮች ለይተህ ጻፍ።

2. ሙሴና ሕዝቡ የመባቸውንና የሥራቸውን ፍሬ ሲያዩ ደስታቸውንና ተስፋቸውን ለመግመት ሞክር።

3. በሥራህ ምን ደስታና ተስፋ አለህ? ለምን?

39፥8 የደረቱ ኪስ፤ እዚህ ኡሪምና ቱሚም አልተጠቀሱም፥ ምናልባት ከተፈጥሮ የተገኙ በመሆናቸው ይሆናል (28፥30)።

ሳምንት 25 ቅዳሜ

ኦሪት ዘጸአት 40፥17-38

መግቢያ፤ ከአንድ ዓመት ሥራ በኋላ የመገናኛው ድንኳን ሲተከል ተዘጋጀ፤ አሁን ሙሴና ሕዝቡ እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ እያንዳንዱን ዕቃ በቦታው ሲያስቀምጡ፥ ደስታቸውና ተስፋቸው ከፍ ያለ እንደነበረ አይጠረጠርም።

1. በንድፉ የሚገኙትን የዕቃዎች ስም ከቍጥሮቻቸው ጋር ጻፍ (ቍ.17-33)።



2. እግዚአብሔር ሥራውን በምን አኳኋን ባረከ(34-35)?
3. እግዚአብሔር እስራኤልን በጉዞአቸው ሁሉ እንዴት መራቸው (36-38)?
4. ከእግዚአብሔር ጋር የምትገናኝበት ልዩ ስፍራ አለህን?
5. እግዚአብሔር እንዴት ይመራሃል?
6.* የመገናኛውን ድንኳን፥ ሊቀ ካህናትን፥ ካህናትን ከነልብሳቸው በዓይነ ልቡናህ ለማየት ሞክር፤ ውበታቸውንና ክብራቸውን ሁሉ ከዕብራውያን 8፥4-5፤ 9፥8-10 ጋር አስተያይተህ የምን ምሳሌ እንደሆኑ አስተውል።

በይበልጥ ስለ መገናኛ ድንኳን ሁኔታ ምሳሌነት ለማወቅ ስትፈልግ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት «የእግዚአብሔር ማደሪያ» የሚለውን ተመልከት።

ሳምንት 26 እሑድ — መዝሙር 25(26)

መግቢያ፤ ዳዊት የመገናኛ ድንኳኑንና ሥርዓቱን ከልብ በመውደዱ ሃይማኖቱ እውነተኛ መሆኑን ያሳያል።

1. በቁ.1-5 ስለ ዳዊት ጠባይ ምን ተገልጧል?
2. ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት የልቡን ቅንነት ምክንያት አድርጎ ሊያቀርብ፥ ኃጢአተኛ እንዳልሆነ ያስብ ነበርን(1፥11)? በምን ታውቃለህ (11)?
3. ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤት ከልብ እንደወደደ በምን ይታያል (6-8፥12)?
4. አንተ፥ ሀ)ወደ እግዚአብሔር ቤት (ወደ ቤተ ክርስቲያን) ስትሄድ ምን ይሰማሃል?፥ ለ) ከእግዚአብሔር ቤት ጋር ያለህ ግንኙነት በጠባይህ ላይ ምን ለውጥ ያመጣል?

ቁ.6 እጆቼን በንጽሕና አጥባለሁ፤ በመገናኛው ድንኳን አደባባይ በመሠዊያውና በተቀደሰው ድንኳን መካከል ትልቅ መታጠቢያ ሳሕን ይቀመጥ ነበር፤ ወደ ድንኳኑ ወይም ወደ መሠዊያው ሳይቀርቡ ካህናት እጃቸውንና እግራቸውን እንዲታጠቡ ትእዛዝ ተሰጣቸው (ዘጸ.30፥17-21) ዳዊት በዚህ ሥርዓት መንፈሳዊ ትምህርትን እንዳገኘ ይታያል።

ሳምንት 26 ሰኞ — ሉቃስ 19፥29-48

መግቢያ፤ ኢየሱስ የምስት ዓመት አገልግሎቱን ከፈጸመ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ለሕማማቱ ወጣ።

1. ኢየሱስ በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በመግባቱና ቤተ መቅደስን በማንጻቱ ምን ገለጠ (ዘካ.9፥9፤ ኢሳ.56፥7፤ ኤር.7፥11 ተመ.)?
2. ደቀመዛሙርቱና ተራው ሕዝብ ኢየሱስን በምን አኳኋን ተቀበሉ (ቁ.37-38፡47-48) ለምን?
3. ፈሪሳውያንና ሌሎች መሪዎች በኢየሱስ ለምን አልተደሰቱም (39፡45-48)?
4. ኢየሱስ በብዙ ደስተኞች መካከል ሲገኝ ለምን አለቀሰ (39-47)?
5. ይህ አንቀጽ ስለ መዳን ቀን ምን ያስተምራል (41-46)?

6. ዛሬ ሰዎች ስለ ሰላም ምን ያህል ያስተውላሉ?

ቍ.29 ደብረ ዘይት በሚባል ተራራ፤ ከተራራው ፊት ለፊት ጥልቅ ከሆነው ከቄድሮን ሸለቆ በላይ ኢየሩሳሌም በግልጥ ትኳኃን ይታያል።

ቍ.39 ገሥጻቸው (ዝም አሰኛቸው)፤ ፈሪሳውያን ኢየሱስን እንደ መጪሕ አልተቀበሉትም ነበርና የሮም መንግሥት ከሕዝቡ እንቅስቃሴ የተነሣ ከባድ እርምጃ እንዳይወስድባቸው ይፈሩ ነበር።

ቍ.42-44 የሮም ሠራዊት ኢየሩሳሌምን በ 70ዓ.ም ሲያፈርስ ብዙ ሰዎች አለቁ።

ቍ.45 የሚሸጡትና የሚገዙት፤ በተለይ ለመሥዋዕት የሚታረዱ እንስሳት።

ሳምንት 26 ግክሰኛ ሉቃስ 20፥1-26

1. የቤተ መቅደስ ባለሥልጣኖች ኢየሱስን ስለ ሥልጣኑ እንዲጠይቁት የገፋፋቸው ምን ነበረ(19፥45-46)?
2. ለኢየሱስ ጥያቄ (ቍ.4) ትክክለኛ መልስ ቢሰጡ ኖሮ፥ ለራሳቸው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ማግኘት እንዴት ይችሉ ነበር?
3. የወይኑ አትክልት ገበሬዎችን ምሳሌ ከእስራኤል ታሪክና ሁኔታ ጋር አስተያይ (9-16)።
4. ኢየሱስ አሁን ስለ ራሱ በገሐድ ምን አስተማረ (13-15፡17-18)።
5. ሰው ለሁለት መንግሥት ተጠቂነት ለምን ይኖረዋል (25)? በሁለቱም የሚገባህን ትፈጽማለህን?
6. ኢየሱስን የተቃወሙትን ሰዎች ጠባይ በምስት ቃላት ለመግለጥ ሞክር፤ ዛሬ ወንጌልን የሚቃወሙት እንደ እነዚህ ያሉት ናቸውን?

ቍ.1 ሽማግሌዎች፤ ከዋና ካህናትና ከሕግ መምህራን ጋር በአይሁድ ሸንጎ መንበር የነበራቸው የታወቁና ሀብታም አይሁድ።

ቍ.9-16 ኢሳ.5፥1-7፤ሉቃ.11፥46-52፤ 13፥32-35፤19፥42-44 ተመ.።

ቍ.17 ድንጋይ፤ በመዝ.117(118)፥2 በወቅቱ በነበሩት መንግሥታት የተናቀረውን የእስራኤል ንጉሥ ወይም የእስራኤል ሕዝብ ያመለክታል፤ ኢየሱስ እውነተኛው የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ በኢሳ.28፥14-16 መሠረት ስለ ራሱ እንደተጻፈ ተረጐመው።

የማዕዘን ራስ ሆነ፤ በመዝ.117(118)፥22 በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ እስራኤል ዋናውን ስፍራ እንደሚይዝ አሳየ (ኢሳ.28፥16)፤ አሁን ግን ኢየሱስ በእስራኤል መሪዎች አማካይነት በመገደሉና ፥ ከሙታንም ተለይቶ በመነሣቱ የሰው ደኅንነት ዐቢይ ቦታ እንደሚኖረውና የሚድኑት ሁሉ በእርሱ መሠረትነት እንደሚኸኩ ተረጐመው (ሐ.ሥ.4፥11-12፤ኤፌ.2፥20፤ 1ጴጥ.2፥4-6)።

ቍ.18 ይፈጨዋል (ይጨፈለቃል)፤ ከክርስቶስ ጋር የግይገጣጠሙትን በፍርድ ያጠፋቸዋል (ኢሳ.8፥14-15፤ዳን. 2፥34-35፡44፤ሮም 9፥32-33)።

ቍ.22 ለቄሣር ግብር ልንሰጥ ተፈቅዶአልን? ተንኰል የሞላበት ጥያቄ ነበረ፤ ምክንያቱም «አይፈቀድም» ቢል ኖሮ፥ ይከሱት ነበር፤ «ይገባል» ቢል ደግሞ በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ ይጠላ ነበርና።

ቍ.24 የቄሣር ነው፤ በግለታቸውና በሮም መንግሥት ገንዘብ በመጠቀማቸው፥ እነርሱ ቄሣር በእስራኤል ላይ ባለመብት መሆኑን ከግረጋገጥ አልጻኑም ነበር።